# ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ

# ፕሮግራም

(በፓርቲው መስራች ጉባኤ የፀደቀ)

መጋቢት 2011
አዲስ አበባ

# ማውጫ


**መግቢያ** ...... **1**

**1 የፖለቲካ ፕሮግራም** ...... **6**

1.1 የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም ...... 6

1.2 መሰረታዊ ሙብቶች ...... 6

1.3 የመንግስት አወቃቀር ...... 7

1.4 ስርዓተ-መንግስት ...... 7

1.5 ሕገ-መንግስት ...... 7

1.6 የመንግስት አካላት ...... 8

1.7 ሀገር መከላከል፣ ፖሊስና የሀገር ደህንነት ...... 8

**2 የኢኮኖሚ ፕሮግራም** ...... **10**

2.1 አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዓላማዎች እና መርሆች ...... 10

2.2 ግብርናና ገጠር ልማት ...... 11

2.3 የአርብቶ-አደር ልማት ...... 13

2.4 የመሬት ይዞታ ...... 14

2.5 መሰረተ-ልማት ...... 15

2.6 ንግድ እና ኢንቨስትመንት ...... 16

2.7 ቱሪዝም ...... 17

2.8 አምራች ኢንዱስትሪ ...... 18

2.9 ማክሮ ኢኮኖሚ ፕሮግራሞች ...... 19

**3 ማህበራዊ ፕሮግራም** ...... **21**

3.1 ትምህርት ...... 21

3.2 ጤና ...... 23

3.3 ከተማና ቤቶች ልማት ...... 24

3.4 ወጣቶች ...... 26

3.5 ሴቶችና ህጻናት ...... 27

3.6 ኃይማኖት ...... 29

3.7 ስፖርት ...... 30

3.8 የአካባቢ ጥበቃ ...... 31

**4 የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ** ...... **32**

4.1 የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መርሆች ...... 32

4.2 ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖረን ግንኙነት ...... 33

4.3 ከአፍሪካ ህብረት እና ከአባል ሀገራቱ ጋር የሚኖረን ግንኙነት ...... 33

4.4 ከሌሎች የዓለም ሀገራት እና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚኖረን ግንኙነት ...... 33

እዝል የነፃነትና እኩልነት ፓርቲ መዝሙር ...... 34

## መግቢያ

በ18ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የተጀመረው የኢንዱስትሪ አብዮት በየምዕተ ዓመቱ ፍጥነቱን እየጨመረና አድማሱን እያሰፋ አብዛኛውን የዓለም ሀገራት ያካተተ ሲሆን በዚህም አፍሪካን ጨምሮ ብዛት ያለው የዓለማችን ህዝብ የኑሮ ደረጃ እንዲሻሻል ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡የኢንዱስትሪ አብዮቱን ያቀጣጠለው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፈጣን እድገት በሀገሮችና በሰዎች ላይ አዎንታዊ እና አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ በአንድ በኩል በሀገሮች፣ በህብረተሰብ፣ በድርጅቶችና በግለሰቦች መካከል ያለውን ርቀት በእጅጉ እንዲቀንስ፣ ዓለም አቀፍ ንግድ እንዲስፋፋ፣ የዓለም የጤና ደረጃ ከፍ እንዲል፣ አማካኝ የነፍስ ወከፍ ገቢ እንዲጨምር፣ የትምህርት ተሳትፎ እንዲያድግ፣ ጎጂ ባህሎችና እምነቶች እንዲቀንሱ፣ የሴቶች ሁለንተናዊ ተሳትፎ እንዲያድግ እና በሌሎች በርካታ ጉዳዮች ላይ ገንቢ ሚና ተጫውቷል፡፡ በሌላ በኩል በሀገሮችና በዜጎች መካከል የሀብትና የገቢ ልዩነት እንዲሰፋ፣ አካባቢ እንዲበከልና እንዲጎሳቆል፣ አውዳሚ ግጭቶችና ጦርነቶች እንዲበራከቱ፣ የፖለቲካ አለመረጋጋቶች እንዲባባሱ፣ ግለኝነት እንዲገን፣ ያልተመጣጠነ የህዝብ እድገትና ፍልሰት እንዲበራከት፣ ብሄርተኝነት እንዲስፋፋ፣ የቤተሰብና ማህበረሰብ መስተጋብርና ግንኙነት እንዲላላ፣ ስራ አጥነት እንዲጨምርና ወንጀል እንዲበራከት፣ ተደጋጋሚ የገንዘብና የምጣኔ ሀብት ቀውስ እንዲፈጠር . . .ወዘተ ምክንያት ሆኗል፡፡ በአፍሪካ፣ እስያ፣ ደቡብ አሜሪካና የበለጸጉ በሚባሉ የአውሮፓና የአሜሪካ ሀገሮች ሳይቀር አስከፊ ድህነት ነግሷል፡፡ የዓለማችን ግማሽ የሚሆነው ሀብት ከዓለም ህዝብ አንድ ከመቶ በማይበልጡ ባለሀብቶች ቁጥጥር ስር ሲሆን፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ ታዳጊ ሀገራት ከጠቅላላው ዜጎች አንድ ከመቶ የማይበልጡ ባለሀብቶች የየሀገራቱን 90 ከመቶ በላይ ሀብት ተቆጣጥረው ይገኛሉ፡፡

ሉላዊነት (Globalization) በፍጥነት እያደገ በሚሄድበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን በሀገራችን የሚስተዋሉ ውስብስብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችና ተግዳሮቶች የተወሰኑት ዓለም ዓቀፍ ገጽታ ሲኖራቸው ቀሪዎቹ ሀገር በቀል እና የሀገራችን የፖለቲካና ማህበራዊ ታሪክ፣ አስተሳሰብና ግንኙነት የወለዷቸው ናቸው፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** (**ነእፓ**)የሀገራችን እና የህዝባችን ችግሮች ምንጭ በዋናነት ፖለቲካዊ እንደሆነ እና መፍትሄውም በአብዛኛው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ እንደሆነ ያምናል፡፡ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ አግላይ የፖለቲካ ስርዓት፣ ማኅበራዊ ፍትህ መጥፋት፣ አድሎ፣ ወገንተኛነት፣ ብሄርንና እምነትን መሰረት ያደረጉ ልምዶችና አሰራሮች የሀገራችን የፖለቲካ ስርዓት መገለጫዎች ሆነው ብዙ ዘመናት አልፈዋል፡፡ የዘር፣ የጎሳና የኃይማኖት ብሄርተኝነት ህዝባችንን ከፋፍሎ አንድነታችንን አላልቶታል፡፡ ለታሪካችን ያለን ቦታና አረዳድ እጅግ የተራራቀ ሲሆን ታሪካዊ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ልዩነቶቻችን እየሰፉ መጥተዋል፡፡ በታሪካዊ ጉዳዮች ዙርያ ገንቢ ያልሆኑ ክርክሮች ተበራክተው የመላው ህዝባችን መሰረታዊ ችግር በሆኑት ድህነት፣ ስራ አጥነት፣ ረሀብ፣ ስደት ወዘተ ላይ በርትተን እንዳንሰራ ኃይላችንን ከፋፍሎታል፡፡

ነጻና ገለልተኛ የፍትህ ስርዓት መጥፋት፣ ስራ አጥነትና ድህነት፣ የመሰረተ ልማት እጥረት፣ ማህበራዊ ቀውስ፣ የሀገርና የህዝብ ፍቅር መሸርሸር፣ በዜጎች መካከል በመተማመን ፈንታ ጥርጣሬ መንገስ ከሀገራችን አንኳር ችግሮች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ የንጹህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት፣ የመኖሪያ ቤት፣ የትምህርትና ጤና አገልግሎት፣ በቂ ትራንስፖርትና መገናኛ፣ ፈጣንና ቀልጣፋ የህዝብ አስተዳደር የሀገራችን ህዝብ ህልም እና ምኞት መሆናቸው ዛሬም እንደቀጠለ ነው፡፡ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች መካከል የትምህርት፣ ጤና እና ሌሎች አገልግሎቶች ሽፋን ዝቅተኛ ሲሆን ኢ-ፍትሀዊ ስርጭቱ እየሰፋ መጥቷል፡፡ ዓለም 4ኛ ትውልድ የኢንዱስትሪ እድገት ላይ በደረሰበት ዘመን የሀገራችን ኢኮኖሚ በዝናብ ላይ የተመሰረተ ዝቅተኛ ግብርና እና ደካማ የአምራች ኢንዱስትሪ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ያላቸው የሀገራችን አካባቢዎች እና ህዝቦች አድገውና ለምተው ለሌሎች የሀገራችን ክፍሎችና ዜጎች ኑሮ መሻሻል እና መለወጥ አስተዋጾ ማድረግ ሲችሉ በድህነት እና ኋላ-ቀርነት አዙሪት ውስጥ ይማቅቃሉ፡፡ የሀገራችን ማዕከላዊ ክፍል ከፍተኛ የህዝብ ጥግግት፣ አነስተኛ የነፍስ ወከፍ ገቢ፣ ትንንሽ የእርሻ መሬት ይዞታ፣ ዝቅተኛ ምርታማነት ያለው ሲሆን በአንጻሩ ዝቅተኛ እና የጠረፍ አካባቢዎች አነስተኛ የህዝብ ጥግግት፣ ለሜካናይዝድ ግብርና የሚስማማ ሰፋፊ እና ለም መሬት፣ ለመስኖ ምቹ ወንዞች ያሉበት አካባቢ ነው፡፡ በየትኛውም የሀገራችን ክፍል የሚገኘውን ሀብት መላውን የሀገራችን ህዝብ በሚጠቅም መንገድ ስራ ላይ ለማዋል የሚችል ሰፊ የህዝብ ድጋፍና ተቀባይነት ያለው የመንግስት ስርዓት መገንባት ባለመቻላችን ራሳችንን መመገብ የማንችል የድህነት ተምሳሌት ሆነናል፡፡ ከሀገራችን የቆዳ ስፋት ከ60 በመቶ በላይ በሚገመተው ክፍል የሚኖረው አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ህዝባችን ተገቢ የፖሊሲ ድጋፍ ተነፍጎት በድርቅ፣ በረሃብና በግጭት ውስጥ ይኖራል፡፡

የሀገራችን ህዝቦች ባካሄዷቸው ሰፊ እና ረዥም የፖለቲካ ትግሎች የማይናቅ ድሎችን ማስመዝገብ ቢችሉም በሀገራችን የቆዩት መሰረታዊ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ዛሬም አልተቀረፉም፡፡ በየዘመኑ በትረ ስልጣኑን የጨበጡ አምባገነን መንግስታት በተከተሏቸው የተሳሳቱ የፖለቲካ አመለካከቶችና ፖሊሲዎች ችግሮቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ ሄደዋል፡፡ በተለይም ባለፈው ሩብ ክፍለ-ዘመን በሀገራችን የነገሰው ብልሹ የፖለቲካ ስርዓትና አሰራር በህዝቦች መካከል ግጭትና አለመረጋጋት እንዲበራከት፣ ዘርንና ብሄርን መሰረት ያደረጉ አድሏዊ አሰራሮች እንዲስፋፉ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡ በዚህ ምክንያት በጣም ጥቂት የስርአቱ አባላትና ግብረ አበሮቻቸው በሀገራችን ታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው ሀብትና ንብረት ሲያጋብሱ ሰፊው የሀገራችን ህዝብ በድህነት ውስጥ እንዲኖር ጥቂት የማይባል ወገናችንም ስደትን እንዲመርጥ ተደርጓል፡፡ በዚህም ሳቢያ ግማሽ የሚጠጋ የሀገራችን ህዝብ ከድህነት ወለል በታች ይኖራል፡፡ ስርአቱን ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለመታገል የተንቀሳቀሱ ዜጎቻችን ዘግናኝና ኢ-ሰብአዊ በሆነ አያያዝ ለእስርና ሞት ተዳርገዋል፡፡

ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማረጋጋጥ በርካታ እድሎችና መልካም አጋጣሚዎች ያሏት ሀገራችን ከትውልድ ወደ ትውልድ መሰረታዊ ለውጥና እድገት ሳትጎናጸፍ ኖራለች፡፡ ሀገራችን ሰፊ እና ለማልማት ምቹ የሆነ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ስትሆን ለግብርና ምቹና ለም የእርሻ ቦታዎች፣ ለመስኖ የሚውሉ ወንዞችና ጅረቶች፣ ውብ መልከዓ ምድር አሏት፡፡ኢትዮጵያ በዓለም ብርቅየ የዱር እንስሳትና አዕዋፋት፣ ለቱሪስት መስህብ የሆኑ ተራሮችና ደኖች እንዲሁም እድሜ ጠገብ ቅርሶች መገኛ ናት፡፡ ከግማሽ በላይ የኢትዮጵያ ህዝብ በወጣት የተገነባ ሲሆን ጥራት ያለው ትምህርትና ስልጠና ማግኘት ቢችል ለሀገራችን ሁለንተናዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጾ ማበርከት ይችላል፡፡

የሀገራችን አጠቃላይ ሁኔታ በወፍ በረር ይህንን በሚመስልበት ሁኔታ፣ ብዙ የአፍሪካ ሀገራትና መላው ዓለም በፈጣንና ሁሉን አቀፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና፣ ስትራቴጂያዊ ለውጦች ውስጥ በማለፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ በመረጃ እና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ እድገት የሚመራው የለውጥ ሂደት በሀገራት፣ በህብረተሰብ እና በግለሰቦች መካካል ያለውን ግንኙነት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀየር አድርጓል፡፡ በየግዜው እያደገ የመጣው የሉላዊነት አስተሳሰብ የዓለም ዓቀፍ ንግድ ይበልጥ እንዲስፋፋ የሸቀጥና የአገልግሎት ግብይት እንዲያድግ አስችሏል፡፡ በአፍሪካ ህብረት የበላይ ጠባቂነት በአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠናና የተሟላ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የባህል ትስስር ለመፍጠር የሚካሄደው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

የመንግስት አወቃቀርና አደረጃጀት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራትና የብዙሀን መገናኛ ሚና፣ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አረዳድና አተገባበር በፖለቲካው መስክ ከታዩ አበይት የለውጥ ማሳያዎች ናቸው፡፡ በአፍሪካ አንዳንድ ሀገሮች የተሻለ የፖለቲካ ምህዳር እና ተሳትፎ እድገት የታየ ሲሆን በተቀሩት ሀገሮች የፖለቲካ ምህዳሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠበበ መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች እየነጠፉ፣ የሰብአዊና ፖለቲካዊ መብቶች አያያዝ እያሽቆለቆለ የመጣበት ሁኔታ ይስተዋላል፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ያለው ሁኔታ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** (**ነእፓ**) ሀገራችን ያሉባትን ውስብስብ ችግሮች እንዲወገዱ በጠንካራ ሀገራዊና የህዝብ ፍቅር ተሞልቶ፣ በጥናትና በመረጃ ላይ የተመሰረ ፕሮግራምና የፖሊሲ ማእቀፎችን ቀርጾ የኢትዮጵያን ዘላቂ እድገትና ብልጽግና እውን ለማድረግ የተቋቋመ የፖለቲካ ፓርቲ ነው፡፡ **ነእፓ** በሀገራችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የመልካም አስተዳደር መርሆች እንዲተገበሩ፣ የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥና የፖለቲካ ስልጣን ከህዝብ የሚመነጭበት የፖለቲካ ባህል እንዲሰርጽ፣ ዜጎች ሀሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ ተፈጥሯዊ መብታቸው እንዲከበር፣ የሚዲያና የሲቪል ማህበራት በሀገር ግንባታ ውስጥ ሰፊ ሚና እንዲኖራቸው ይታገላል፡፡ አስተማማኝ ሰላምና ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥ፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች መካከል ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር፣ ለሀገራችን እና ለህዝባችን እድገት **"ነቀርሳ"** ሆኖ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ እድገቷን በማቀጨጭ ላይ የሚገኘው **ሙስና** እንዲወገድ፣ የብሄረሰቦች ቋንቋና ባህል እንዲከበር፣ የሀይማኖት እና የአምልኮ ነጻነትና እኩልነት እንዲረጋገጥ፣ ጾታዊ መድሎ እንዲቆም፣ ሴቶች የትምህርትና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እና በሀገር ግንባታ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በትጋት ይሰራል፡፡

**የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የሀገራችንን ነባራዊና ተጨባጭ የፖለቲካ ሀቆች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ አህጉራዊ እና ዓለም ዓቀፋዊ ለውጦችን በጥልቀት በመመዘን፣ የሀገራችንን ጂኦ-ፖለቲካዊና ስትራቴጂያዊ መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች በመተንተን ፕሮግራሞቹንና ፖሊሲዎቹን አሰናድቷል፡፡ በአንድ በኩል የግዛት አንድነቷ የተከበረ ጠንካራ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ እንዲገነባ በሌላ በኩል የብሄር፣ የቋንቋ፣ የሀይማኖት፣ የባህል ወዘተ ልዩነቶች እንዲከበሩ በማድረግ **ሚዛናዊ** ፖሊሲና የትግል ስልት የሚከተለው ፓርቲያችን የህዝባችንን ውስብስብ እና የረዥም ጊዜ የፖለቲካ ችግሮችና ተግዳሮቶች ለመፍታት ተግቶ ይሰራል፡፡ **የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ከልዩነት ይልቅ አንድነት፣ ከመከፋፋል ይልቅ መሰብሰብ፣ ከጥላቻ ይልቅ ፍቅር፣ ከግጭት ይልቅ ሰላም፣ ከጥርጣሬ ይልቅ መተማመን እንዲሰፍን በመላው የሀገራችን ክፍል ዘላቂ ልማት፣ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት፣ እውነተኛ ወንድማማችነት/እህትማማችነት እንዲነግስ ይሰራል፡፡ የመላው ኢትዮጵያውያን ባህል፣ ቋንቋ፣ ወግ፣ ሃይማኖትና እና ልማዶች በሀገር ደረጃ እውቅና እንዲሰጣቸው ይታገላል፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ሰላማዊ በሆነ የፖለቲካ ትግል እና ነጻ ምርጫ የመንግስት ስልጣን በመያዝ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የውጭ ግንኙነት ፕሮግራሞቹን በተግባር በማዋል የሀገራችንን እድገትና ብልጽግና እውን ለማድረግ ከመላው የሀገራችን ክልሎች በተወከሉ የፓርቲው መስራች አባላት መጋቢት 15 ቀን 2011 ተመሰረተ፡፡

## ራእይ፣ ተልእኮ እና ዓላማዎች

### ራእይ

አስተማማኝ ሰላምና ዘላቂ ኢኮኖሚያዊ እድገት የተረጋገጠባት፣ ዜጎች የዘር፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የሀይማኖት፣ የፖለቲካ አመለካከት ወዘተ ልዩነት ሳይደረግባቸው በብሄራዊ ጉዳዮች እኩል የሚሳተፉባትና ከልማቷ እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑባት የበለጸገችና ዲሞክራሲያዊት ሀገር እውን ሆና ማየት፡፡

## ተልእኮ

መልካም አስተዳደር እና የህግ የበላይነት የተረጋገጠባት፣ የፖለቲካ ስልጣን ከህዝብና ከህዝብ ብቻ የሚመነጭበት የፖለቲካ ባህል የዳበረባት፣ ዜጎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድሎችን ፍትህዊ በሆነ መንገድ የሚጠቀሙባት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት፡፡

## ዓላማዎች

የፓርቲያችን ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፣

1. አካታች እና ዘላቂ ኢኮኖሚ በመገንባት ድህነትን መቀነስ ብሎም ማጥፋት፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፍትህን ማስፈን፣
2. በሀገሪቱ የመንግስት አስተዳደርና መዋቅሮች ውስጥ የመልካም አስተዳደር፣ የግልጸኝነትና ተጠያቂነት ስርአት እንዲጎለብት ማድረግ፣
3. የሰብዓዊና ዴሞክራሲዊ መብቶች እንዲከበሩ ማድረግ፣ የህግ የበላይነትን እውን ማድረግና ነጻ የፍትህ ስርዓት መገንባት፣
4. የብሄሮችና ብሄረሰቦችን ቋንቋና ባህል በእኩልነት ለማበልጸግ፣ ሁሉንም የሀገራችንን ክልሎች ልማት ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ የሚያስችል እውነተኛ የፌደራል ስርአት መገንባት፣
5. አካባቢ መጠበቅ፣ መንከባከብና ማበልጸግ፣ ምቹ የስራ እና የመኖሪያ አካባቢ መፍጠር፣
6. ሳይንስና ቴክኖሎጂን ማስፋፋት፣ በተፈጥሮና ማህበረሰብ ሳይንስ መስኮች ጥናትና ምርምርን መደገፍ፣
7. የገጠር ኢንዱስትሪን ማበረታታትና ማስፋፋት፣ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚውን ማዘመን፣
8. ዜጎች መሰረታዊ አገልግሎቶችን በጥራት፣ በስፋትና በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ፣
9. ሴቶችና ወጣቶች በሀገር ልማት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ እምቅ ኃይላቸውን መጠቀም፣
10. ህጻናት፣ አረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞችና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ዜጎችን መብቶችና ጥቅሞች ማስከበር፣
11. በአፍሪካ ቀንድ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የባህል ትስስርን ማበረታታትና መደገፍ፣ በክልሉ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን አስተዋፅዖ ማድረግ፣
12. ኢትዮጵያ በአፍሪካና በዓለም ዓቀፍ መድረኮች ተሰሚነትና የማይተካ ሚና እንዲኖራት ማስቻል፣ የኢትዮጵያን የውጭ ገጽታ ማሻሻል፡፡

## የትግል ስልቶች

**በመግባባት ላይ የተመሰረተ ከፍጥጫ፣ ከሴራና መጠላለፍ  የራቀ የፖለቲካ ትግል፡** ፓርቲያችን ከማንኛውም የፖለቲካ ኃይል ወይም ድርጅት ጋር በኃላፊነትና በሀገር ፍቅር ስሜት ይሰራል፡፡ ሀገራችንን እና ህዝባችንን በሚጠቅሙ ጉዳዮች ዙሪያ ማንኛውም ዓይነት የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም ወይም ፕሮግራም ካለው የፖለቲካ ድርጅት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

**ሚዛናዊነት እና አካታችነት**፡ የህዝባችንን የብሄር፣ የቋንቋ፣ የሀይማኖት፣ የባህል ብዝሃነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በድርጅታዊ አሰራር፣ በፖሊሲና ፕሮግራም፣ በፖለቲካዊ አቋም፣ ወዘተ ሚዛናዊ እና አካታች መንገድን እንከተላለን፡፡ የግለሰብ ወይም የቡድን መብትና ስሜትን ሊጎዱ ከሚችሉ ድርጊቶች በመራቅ ፓርቲያችን ሁሉንም የሀገራችንን ህዝቦች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ እንዲያካትት ጥረት እናደርጋለን፡፡

**ተፈጥሯዊ ለውጥ፡** በሀገራችን ያለው የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ቢያንስ ላለፉት በርካታ አስርተ-ዓመታት ሲጠራቀሙና ሲደራረቡ የቆዩ በመሆናቸው በአንድ ጀንበር እንደማይቀረፉ ፓርቲያችን ይገነዘባል። በመሆኑም

በሀገር ደረጃ እንዲመጡ የሚፈለጉ ለውጦች የማህበረሰቡን የእድገት ደረጃ በጠበቀ መልኩ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ለመቀየር እንሰራለን፡፡

**አብሮ ማሸነፍ**፡ እውነተኛ ማሸነፍ የሀገር እና የህዝብ ማሸነፍ መሆኑን **ነኢፓ** ይረዳል፡፡ በመሆኑም በፖለቲካ እንቅስቃሴአችን ከድርጅታዊ ድል እና ስኬት ይልቅ የሀገርንና የህዝባችንን ድልና ስኬት እናስቀድማለን፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የፓርቲያችን ውጤታማነትና ስኬት በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ውድቀት ላይ ሳይሆን አብሮ በማደግ እውነተኛ የአጋርነት ስሜት ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

**ህዝብን ማገልገል፡** የአንድ የፖለቲካ እንቅስቃሴና የፖለቲካ ስልጣን ትልቁና የመጨረሻ ግብ ሀገርንና ህዝብን ማገልገል ነው፡፡ ህዝብን እንዲያስተዳድሩ የሚወከሉ የፓርቲና የመንግስት ኃላፊዎች፣ አስተዳዳሪዎችና ቢሮክራቶች ከድሀው ህዝብ "ከእጅ ወደ አፍ" ገቢ ከሚሰበሰብ ግብር የሚከፈላቸው ናቸው፡፡በመሆኑም በየትኛውም የኃላፊነት ደረጃ የሚገኙ የፓርቲያችን አባላት የህዝብ አገልጋይ ሆነው የመስራት ግዴታ ይኖርባቸዋል፡፡

**እውነተኛነት እና ታማኝነት፡** ኢትዮጵያውያን ለመልካም ስነ-ምግባር እና ግብረገብነት ከፍተኛ ዋጋ እንሰጣለን፡፡ ህዝባችን በማህበራዊና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ለእውነተኛነት፣ ቅንነት እና ታማኝነት ላቅ ያለ ክብር ይሰጣል፡፡ በመሆኑም የፓርቲያችን ተርታው አባልም ሆኑ አመራሮች ሀገራችንና ህዝባችንን በእውነተኛነት፣ በታማኝነት እና በፍቅር ያገለግላሉ፡፡

**በትብብር መስራት፡ ነኢፓ** የዴሞክራሲ ስርዓትን ለመገንባት፣ ሀገራዊ መግባባትን ለማጠናከር፣ ጤናማ የፖለቲካ ውድድርን እውን ለማድረግ፣ የሀገራችንን የፖለቲካ ፓርቲዎች አቅም ለመገንባት ብሎም የፓርቲያችንን ራእይና ዓላማዎች በተሻለ ሁኔታ ለማሳካት የሚያግዝ ሆኖ ሲገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ ከተመዘገቡ እና እውቅና ካላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመቀናጀት ይሰራል፡፡ ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሚፈጠሩ የትብብር መድረኮችና ቅንጅቶች የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የሀገሪቱን ህጎች መሰረት ያደረጉ ይሆናል፡፡

# 1 የፖለቲካ ፕሮግራም

## 1.1 የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም

ከቀዝቃዛው ጦርነት ማብቂያ ጀምሮ የሊብራሊዝም አስተሳሰብ በበርካታ የዓለም ሀገራት ዘንድ ተቀባይነቱ እየጨመረ እንደመጣ ይታመናል፡፡ የሊበራል አስተሳሰብ በዋናነት ለዜጎች የኢኮኖሚና የፖለቲካ ነጻነት ትኩረት የሚሰጥ፣ የመንግስትን መጠንና ጣልቃ ገብነት በመገደብ ዜጎች በግልም ሆነ በጋራ በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ እድል የሚሰጥ ስርአት ነው፡፡ ይህ አስተሳሰብ የተንዛዛ የመንግስት አሰራርን፣ ቢሮክራሲያዊ ንቅዘትን፣ የመንግስትን አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት ለማስቆም፣ ሙስናን በማስወገድ ፈጣንና ቀልጣፋ አሰራር እውን ለማድረግ ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የዜጎችን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብት በተሻለ ሁኔታ ለማስከበር ይረዳል ተብሎ ይገመታል፡፡ የሊበራል አስተሳሰብ ሰፊ ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን፣ እንደ ሀገራት የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ የባህልና የቴክኖሎጂ እድገት ደረጃ በተለያየ መንገድ የሚተገበርና አንድ ወጥ መለኪያ የሌለው መሆኑ፤ እንደ ሀገራቱ ተጨባጭ ሁኔታ ሊስተካከል መቻሉ ተቀባይነቱን ሊጨምር እና አተገባበሩም ምቹ እንዲሆን አስችሏል፡፡

በዚህ መሰረት **የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ራእዩን በተሳካ ሁኔታ እውን ለማድረግና ዓላማዎቹን ለማሳካት የሊበራል አስተሳሰብን ከሀገራችን ሁለንተናዊ እድገት ጋር አዋዶ ነባራዊ እና ተጨባጭ የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ እውነታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት **ለዘብተኛ ሊበራሊዝም** ርዕዮተ ዓለም ይከተላል፡፡ የለዘብተኛ ሊበራል ርዕዮተ-ዓለም የሊበራል አስተሳሰቦችን ከሀገራችን ታሪክ፣ ባህል፣ የህዝቦቿ ስነ-ልቦናና ማህበራዊ ልማዶች ጋር በማዋደድ ሀገራዊ እሴቶችን ለመጠበቅ ምቹ የፖለቲካ ምህዳር እንደሚፈጥር ይታመናል፡፡ የለዘብተኛ ሊበራል አስተሳሰብ ለማህበራዊ እሴቶችና ግብረገብነት እውቅና የሚሰጥ ሲሆን የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ በማድረግ ለላቀ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርም ይጠበቃል፡፡ **ነእፓ** በዋነኛነት ከሚከተለው የለዘብተኛ ሊበራል ርዕዮተ ዓለም በተጨማሪ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሶሻል ዴሞክራትን ጨምሮ ሌሎች ርዕዮተ-ዓለማዊ አስተሳሰቦችን መሰረት ያደረጉ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ርዕዮተ-ዓለምን በተመለከተ ፓርቲያችን የሚከተለው ይህ አሰራር በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ከነገሰው በአንድ ርዕዮተ-ዓለም የመታጠር ጠባብ የፖለቲካ አረዳድ ወጣ ባለ መንገድ ከሊበራል አስተሳሰብ ጋር የማይጋጩ፣ የሀገራችንን የእድገት ደረጃ ታሳቢ ባደረገ መንገድ ለሀገራችን ሁለንተናዊ እድገትና ብልጽግና የሚያግዙ ሰፊ የፖሊሲ አማራጮችን ለማሰብ ይረዳል ተብሎ ይታመናል፡፡

## 1.2 መሰረታዊ መብቶች

1. **የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው ብሎ ያምናል፡፡ ከዚህ መሰረታዊ እምነት በመነሳት በዜጎች መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ እኩል የህግ ዋስትናና ከለላ ያገኛሉ፣ ዜጎች ሰው በመሆናቸው ብቻ የተጎናፀፏቸው መሰረታዊ መብቶች ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ፣ የዜጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲረጋገጡ ይደረጋል፣
2. ኢትዮጵያውያን የዘር፣ የብሄር/ብሄረሰብ፣ የሀይማኖት፣ የጾታ፣ የቋንቋ፣ የአካባቢ፣ የፖለቲካ አመለካከት ወዘተ ልዩነት ሳይደረግባቸው በፈለጉበት አካባቢ የመንቀሳቀስ፣ የመኖር፣ የመስራትና ሀብት የማፍራት መብታቸው በተሟላ ሁኔታ እንዲከበር ይደረጋል፣

3. መላው ኢትዮጵያውያን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው እንዲከበሩና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የደረጃ ልዩነት ሳይደረግባቸው፣ ስለ አገራቸው እኩል የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማቸው የሚያደርጉ ህጎችና አሰራሮች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
4. ዜጎች በሚፈልጉት መልኩ የመደራጀት፤ ሀሳባቸውን የመግለፅ፣ የመፃፍ፣ የመቃወም መብታቸው ሳይሸራረፍ እንዲከበር ይደረጋል፣
5. ዜጎች የአካልና የስነ-ልቦና ደህንነታቸው የህግ ከለላ ያገኛል፣ በህግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ድርጊት በመሳተፍ ምክንያት በፍርድ ቤት ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር ህይወትና ንብረታቸው ይጠበቃል፣ ዜጎች ከፍትህ ስርዓት ውጪ ሊያዙ ብሎም ክስ ሳይቀርብባቸውና ሳይፈረድባቸው ፈጽሞ እንዳይታሰሩ፣ ኢ-ሰብዓዊ እና ክብርን ከሚያጎድል አያያዝ እና ቅጣት እንዲጠበቁ ይደረጋል፣
6. ዜጎች በኃይል ተገደው ማንኛውንም ስራ እንዲሰሩ ወይም ግዴታቸውን እንዲወጡ የሚያደርግ አሰራር አይኖርም፣
7. ኢትዮጵያ  የተቀበለቻቸው ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊና ዴመክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ፡፡

### 1.3 የመንግስት አወቃቀር

ኢትዮጵያ የበርካታ ብሄሮች/ብሄረሰቦች፣ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ ባህሎች፣ ወጎችና ልማዶች፣ ኃማኖቶችና ማህበራዊ እሴቶች ያሏቸው ህዝቦች መኖሪያ ናት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ብዝሃ ህይወት፣ መልክአ ምድር፣ የአየር ጸባይና የአኗኗር ዘይቤዎች ላይ የተመሰረተ የማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ብዝሀነት ያሏት ሀገር ናት፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚዘረጋ የመንግስት አወቃቀር እነዚህን የሀገራችንና የህዝባችንን ተፈጥሯዊ ልዩነቶችና ብዝሀነት ታሳቢ ያደረገ፣ በአንድነት ውስጥ ልዩነትን ማስተናገድ የሚያስችል፣ በመፈቃቀድ፣ በመከባበርና በመቻቻል ላይ የተመሰረተ አንድነትን ለመፍጠር የሚያግዝ መሆን ይኖርበታል፡፡

**ነእፓ** ለዚህ ዓላማው እውን መሆን የተሻለው የመንግስት አወቃቀር የፌደራል ስርአት ነው ብሎ ያምናል፡፡ እውነተኛ የፌደራል መንግስት አወቃቀር ሁሉም የሀገራችን ህዝቦች  በስምምነት በመከባበር ተፈቃቅደው ለመኖር የሚያስችል ምቹ አስተዳደራዊ ስርአት ይፈጥራል፡፡ የሚገነባው የፌደራል ስርአት የአስተዳደር ምቹነትን፣ የህዝብ ፍላጎትን፣ ቋንቋና ባህልን፣ መልከዓ-ምድርንና ሌሎች የጋራ እሴቶችን ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፡፡

### 1.4 ስርዓተ-መንግስት

ፓርቲያችን የሚከተለው የመንግስት ስርዓት ፕሬዚዳንታዊ ይሆናል፡፡ ፕሬዝደንቱ (ርዕሰ ብሄር) በቀጥታ በህዝብ የሚመረጥ ሲሆን ለአምስት ዓመታት ያገለግላል፡፡ አንድ ፕሬዝደንት ለሁለት ዙር መወዳደር ይችላል፡፡

### 1.5 ሕገ-መንግስት

ሕገ-መንግስት የዜጎችን መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም የመንግስትን አወቃቀርና አሰራር የሚወስኑ መሰረታዊ ህጎችና መርሆችን የሚይዝ የህግ እና የፖለቲካ ሰነድ ሲሆን በአንድ ሀገር ውስጥ የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ፖሊሲዎች ወዘተ መነሻ ነው፡፡ሕገ-መንግስት መሰረታዊ የሆኑ የፖለቲካ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የውጭ ግንኙነት መርሆችን የሚይዝ ለአንድ ሀገር ሰላምና ብልጽግ እንዲሁም ለዜጎች ዴሞክራሲያዊ አንድነት፣ ነጻነት፣ እኩልነትና ፍትህ ዋስትና የሚሰጥ የዜጎች የመግባቢያ ሰነድ ነው፡፡ሕገ-መንግስት እንደ ስሙ የሀገርና የመንግስት ህግ ይሆን ዘንድ በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ተቀባይነት ያለው፣ ግልጽና የማያሻማ ሊሆን  ይገባል፡፡ ከዚህ አንጻር የሀገራችንን ሕገ-መንግስት ስንመለከተው መስተካከል ያለባቸው ጉዳዮች እንዳሉ እንገነዘባለን፡፡ በመሆኑም **ነእፓ** በስራ ላይ ያለው የሀገራችን ሕገ-መንግስት የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ዉስጥ በማስገባት መሻሻል አለበት ብሎ ያምናል፡፡

1. ሕገ-መንግስቱ የሀገራችንን ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት የሚያስከብር፣ ብሄራዊ ጥቅሞቻችንን የሚያስጠብቅና ሀገራችን ካለችበት ዝቅተኛ የኢኮኖሚ እድገትና አስከፊ ድህነት በፍጥነት እንድትላቀቅ በሚያስችል መልኩ ሊቃኝ ይገባል፣
2. የዜጎቻችንን ሰላምና ደህንነት የሚሸረሽሩ፣ መገንጠልና መለያየትን የሚጋብዙ አንቀጾች ብሄራዊ መግባባትን፣ አብሮነትና ወንድማማችነትን በሚያጠናክር መልኩ ሊሻሻሉ ይገባል፣
3. የሕገ-መንግስት አንዱ ባህሪ ለረዥም ጊዜ ማገልገል መቻሉ ነው፡፡በመሆኑም ከሀገራችን የእድገት ደረጃ ጋር በየጊዜው ሊቀየሩ የሚገቡ ድንጋጌዎችን በሕገ-መንግስት ውስጥ ማካተት ህገ-መንግስቱ ወሳኝ የሆኑ ሀገራዊ ለውጦችን ማስተናገድ እንዳይችል በማሰር በአፈጻጸም ላይ ችግር ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም በየጊዜው ሊቀየሩ የሚገባቸውን አንቀጾች ከህገ-መንግስቱ ማውጣት ያስፈልጋል፣
4. ሕገ መንግስት የአንድ ሀገር ዜጎች የጋራ ሰነድ በመሆኑ የአብዛኛውን ህብረተሰብና የፖለቲካ አስተሳሰብ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ በሀገራችን እስከ ዛሬ በስራ ላይ የዋሉ ሕገ-መንግስቶች በጊዜው የነበሩ መንግስታት የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለምና የፖለቲካ ፕሮግራም ቅጅ ስለነበሩ ፓርቲ እና መንግስትን መለየት አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በስራ ላይ ያለው ሕገ-መንግስተ ከገዥው ፓርቲ ርዕዮተ-ዓለምና የፖለቲካ ፕሮግራም ተለይቶ በሀገሪቱ ያሉ የፖለቲካ ኃይሎችን አስተሳሰብና ፕሮግራም ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ሊሻሻል ይገባል፣
5. ቋንቋ፣ ባንዲራ፣ የክልሎች አመሰራረትና ወሰን የመሰሉ አሻሚና አላስፈላጊ ልዩነቶችና ግጭቶችን ሊፈጥሩ የሚችሉ ጉዳዮች ህገ-መንግስቱ ግልጽና የማያሻማ መልስ ሊሰጥ በሚችል መልኩ ሊስተካከል ይገባል፣

## 1.6 የመንግስት አካላት

የፌዴራል መንግስትና የክልል አስተዳደሮች ሶስት የስልጣን አካላት ይኖራቸዋል፡፡ እነሱም የህግ አውጪ፣ ህግ አስፈፃሚና ህግ ተርጓሚ ናቸው፡፡ ሶስቱ የስልጣን አካላት እያንዳንዳቸው በህገ-መንግስት የሚወሰን ግልፅ ኃላፊነትና ስልጣን ይኖራቸዋል፣ ሶስቱ የስልጣን አካላት በነጻነትና በቅንጅት ይሰራሉ፣ የስልጣን መደራረብና ጣልቃ ገብነት እንዳይኖር የሚያደርግ መስተጋብር ይኖራል፡፡

### 1.6.1 የመንግስት የስራ ቋንቋ

አማርኛና ኦሮምኛ የፌዴራል መንግስት የስራ ቋንቋ ይሆናሉ፡፡ የፌደራል መንግስቱ አካል የሆኑት የክልል መስተዳድሮች በክልሉ ውስጥ በስፋት ከሚነገሩ ቋንቋዎች ውስጥ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ቋንቋዎች የክልል መስተዳድሩ የስራ ቋንቋ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ፡፡

## 1.7 ሀገር መከላከል፣ ፖሊስና የሀገር ደህንነት

### 1.7.1 የሀገር መከላከያ ኃይል

1. ለህዝብና በህዝብ ለተመረጠ መንግስት ታማኝ የሆነ፣ ለሀገሪቱ ህገ-መንግስት ዘብ የሚቆም፣ ሀገራችንን ከማናቸውም አይነት የውስጥና የውጭ ጥቃት የሚከላከል የመከላከያ ኃይል ይገነባል፣
2. የሀገር መከላከያ ኃይል ዋነኛ ተልዕኮ ሀገርና ህዝብን መጠበቅ፣ የሀገርን ዳር ድንበርና ሉአላዊነት ማስከበር ይሆናል፣
3. የሀገራችን ምጣኔ ሀብት በሚፈቅደው መጠን ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የታጠቀ የመከላከያ ኃይል ይገነባል፣
4. የመከላከያ ሰራዊት አባላትና አመራር ስብጥር ሁሉንም የኢትዮጵያ ህዝቦች ያማከለ እንዲሆን ይደረጋል፣ የሀገር መከላከያ ኃይላችን የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል አመኔታ፣ ድጋፍ እና ተቀባይነት ማግኘት ይችል ዘንድ ጠንካራ ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው ይደረጋል፣

5. የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል ሳይሆኑ፣ ተጠሪነታቸው በህዝብ ለሚመረጥ መንግስት ብቻ ይሆናል፣
6. የኢትዮጵያ መከላከያ ኃይል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለጎረቤት ሀገሮች፣ ለአፍሪካና ለዓለም ሰላም እና መረጋጋት ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶችንና ህጎችን በጠበቀ ሁኔታ ተሳትፎ ሊያደርግ ይችላል፣
7. የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላትና አመራር ለሀገርና ለህዝብ ያላቸውን ውለታ ታሳቢ ያደረገ ልዩ የጉዳትና የህይወት ካሳ ይከፈላል፣ ሀገራዊ ግዳጅ በመወጣት ላይ ሳሉ ለሚሰዉ የሰራዊቱ አባላት ቤተሰቦች መንግስት ተገቢውን እንክብካቤና ድጋፍ ያደርጋል፣
8. የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላትና ልዩ ልዩ ተቋማት በአስቸኳይና ድንገተኛ አደጋ ወቅት መንግስት ለሚያካሂደው የነፍስ አድን ዘመቻ በቂ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

### 1.7.2 የፖሊስና ደህንነት ኃይል

1. ሙያዊ ብቃት ያለው፣ በስነ-ምግባር የታነፀ፣ ህግ የሚያከብርና የሚያስከብር፣ ከማናቸውም ዓይነት ወገንተኝነት የፀዳ ለህገ-መንግስቱ ታማኝ የፖሊስ ኃይል በፌደራልና በክልል ደረጃ ይገነባል፣
2. የፖሊስ ሰራዊቱን ገለልተኝነት ለመጠበቅና ለአሰራር አመች ይሆን ዘንድ፣ የፖሊስ ሰራዊት አባላት የፖለቲካ ፓርቲ አባል አይሆኑም፣
3. በየደረጃው ያለው የፖሊስ ሰራዊት ተቋማት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚወክሉ እንዲሆንና ዋነኛ ተልዕኮውም በህግ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ የሚወጣ ተቋም እንዲሆን ይደረጋል፣
4. የደህንነት ተቋሙ የሀገርንና የህዝብን ፍላጎት መሰረት አድርጎ የሚዋቀር ሲሆን ዋና ዓላማው ሰላምን ሊያደፈርሱ የሚችሉ ስጋቶችንና ሀይሎችን ቀድሞ በመለየት የህግ የበላይነትና የህዝብን ሰላም ማስከበር ነው፡፡
5. የሀገር ደህንነት ተቋም የየትኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባል ባልሆኑ አባላትና አመራሮች የተደራጀ፣ የየትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የበላይነት የማይንጸባረቅበት ተቋም እንዲሆን ይደረጋል፡፡

# 2 የኢኮኖሚ ፕሮግራም

**ምጣኔ ሀብታዊ እውነታዎች**

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአፍሪካና በዓለም ከሚገኙ ድሀ ሀገራት አንዷ ስትሆን ግማሽ የሚጠጋው የሀገራችን ህዝብ ከድህነት ወለል በታች ይኖራል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ስታትስቲካዊ መረጃ እንደሚያመለክተው በአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት (GDP) ሀገራችን ከአፍሪካ 7ኛ፣ ከዓለም 71ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች፡፡ በአንጻሩ ኢትዮጵያ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘውን ምጣኔ ሀብቷን በፍጥነት ለማሳደግ የሚያስችሏት ሰፊ እና ጥቅም ላይ ያልዋሉ የተፈጥሮ ሀብቶች በብዛት ያላት ሀገር ናት፡፡ የከርሰ ምድር ሀብቶች፣ ማዕድናት፣ ለግብርና ምቹ የአየር ንብረት፣ በርካታ ወንዞችና የከርሰ ምድር ውሀ፣ ወጣትና በአምራች እድሜ ላይ ያለ የሰው ኃይል ከብዙ በጥቂቱ ይገኙበታል፡፡ የግብርናው ዘርፍ የሀገራችን ኢኮኖሚ ምሰሶ ሆኖ ዛሬ ድረስ የዘለቀ ሲሆን ከፍተኛ የስራ ዕድል በመፍጠር እና የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ትልቁን ድርሻ ይይዛል፡፡

በሀገራችን የአገልግሎ ዘርፉ በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ሲሆን ለአጠቃላይ ብሄራዊ ምርት ያለው ድርሻ ከግብርናው ዘርፍ በልጧል፡፡ የአገልግሎት ዘርፉ ለዜጎች የስራ ዕድል በመፍጠርና እና የውጭ ባለሀብቶችን በመሳብ ያለው ድርሻ በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል፡፡ በአንጻሩ የሀገራችን የኢንዱስትሪ ዘርፍ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በአብዛኛው ጥሬ ሀብትንና የግብርና ምርቶችን በማቀነባበር፣ በጨርቃጨርቅና በአግሮ ኢንደስትሪ ምርቶች ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ዘርፉ ለሀገራችን ኢኮኖሚ የሚኖረውን አስተዋፅዖ ከፍ ለማድረግ ከግብርናና አገልግሎት ሰጭ ዘርፎች ጋር ያለውን ትስስር ማሳደግ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማፋጠን ኢኮኖሚያችን ወደ ዘመናዊና ኢንዱስትሪ-መር ኢኮኖሚ እንዲሸጋገር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## 2.1 አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዓላማዎች እና መርሆች

ሀገራችን ያሏትን ዕድሎችና መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም ዘላቂ፣ አረንጓዴ፣ በአፍሪካ እና በዓለም ተወዳዳሪ ጠንካራ ኢኮኖሚ መገንባት የፓርቲያችን ዋና የኢኮኖሚ ዓላማ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

1. ዜጎች ለኑሮ የሚያስፈልጓቸው መሰረታዊ ፍላጎቶች ተሟልተውላቸው የተረጋጋ እና ደስተኛ ኑሮ መኖር ይችሉ ዘንድ በቂ የነፍስ ወከፍ ገቢ እንዲኖራቸው ማስቻል፣
2. አስከፊ ድህነትን መቀነስ ብሎም ማጥፋት፣
3. በዜጎችና በክልሎች መካከል ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር ማስቻል፣
4. ስራ አጥነትንና የዋጋ ግሽበትን በመቆጣጠር በሀገራችን ኢኮኖሚ ላይ የረዥም ጊዜ አፍራሽ ተፅዕኖ ሊያደርስ የሚችል የኢኮኖሚ መዋዠቅን መከላከል እና የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እንዲኖር ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር፣
5. የሀገራችንን የምጣኔ ሀብት ዕድገት ታሳቢ ያደረገ ኢኮኖሚያዊ የመዋቅር ሽግግር መፍጠር፣
6. የኢኮኖሚ እድገትን ከአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ጋር በማቆራኘት የአረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት፣

**ስልቶች**

ከላይ የተጠቀሱ ምጣኔ ሀብታዊ ዓላማዎችን እውን ለማድረግ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የሚከተሉትን ስልቶች ይጠቀማል፡፡

1. ኢንቨስትመንትን ቀላልና የተቀላጠፈ በማድረግ የሀገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስተሮች መዋዕለ-ንዋያቸውን በተቀላጠፈ መንገድ ስራ ላይ እንዲያውሉ ማድረግ፣

2. ለኢኮኖሚ ልማት እንቅፋት እና አሳሪ የሆኑ ህጎችን በማስወገድ በምትካቸው ቀላል እና ለአተገባበር ምቹ ህጎችን ማውጣት፣ ሙስናና ኪራይ ሰብሳቢነትን መዋጋት፣
3. ፍትሀዊና ግልጽ የግብር ስርዓት መዘርጋት፣
4. መንግስት ለዜጎችና ድርጅቶች ለኢኮኖሚ ልማት ጠቃሚ በሆኑ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ማበረታቻ መስጠት፣
5. የተዝረከረከ እና የተጓተተ አሰራርን በማስቀረት በቴክኖሎጂ የታገዘ ቀልጣፋ አሰራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
6. የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲና ፕሮግራሞችን ከሀገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተናበቡ እንዲሆኑ ማድረግ፣
7. የውጭ ብድርና እርዳታን መቀነስና አቅም በፈቀደ መጠን በራስ አቅም ላይ መወሰን፣
8. የህዝብ ዕድገትን ከኢኮኖሚ ልማት ጋር እንዲጣጣም በማድረግ የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል፣
9. የፋይናንስ ዘርፉን የብድር ስርዓት አስተዳደር በማጠናከር የገንዘብና የኢኮኖሚ ቀውስን አስቀድሞ መከላከል፣
10. ምጣኔ ሀብታዊ መረጃዎች በተፈለገበት ጊዜና ቦታ በቀላሉ እንዲገኙ ማስቻል፣
11. ከጎረቤት ሀገሮችና ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ጋር ጠንካራ የኢኮኖሚና የንግድ ትስስር መፍጠር፣
12. ግብርና፣ ኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎችን በማቀናጀት ምርትንና ምርታማነትን ማሳደግ፣
13. ለባለሀብቶችና ኢንቨስተሮች የንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ዋስትና መስጠት (Property right)፣
14. የቁጠባ ባህልን በማዳበር ለኢንቨስትመንት በቂ ሀብት ከሀገር ውስጥ ማመንጨት የሚቻልበትን ሁኔታ መፍጠር፡፡

**የመንግስት ሚና**

**ነእፓ** የኢኮኖሚ ዓላማዎቹን ለማሳካት በመሰረታዊነት ገበያ-መር የኢኮኖሚና የንግድ ስርአትን የሚከተል ሲሆን፣ የሀገሪቱን ልማት ለማፋጠንና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ የመንግስት ተሳትፎ አስፈላጊ በሚሆንባቸው ሁኔታዎች መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ያለውን ኃላፊነት ይወጣል፡፡ መንግስት በኢኮኖሚ ውስጥ እንዲሳተፍ የሚያስገድዱ ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. ከፍተኛ የግንባታ መዋዕለ ንዋይ የሚፈልጉ እና ዝቅተኛ የትርፍ መጠን ያላቸው፣ ለግል ባለሀብቶች አዋጭ ወይም ሳቢ ያልሆኑ ግዙፍ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችን መንግስት በብቸኝነት ወይም ከግሉ ዘርፍ ጋር በሽርክና ይገነባል፡፡ የየብስ እና የባቡር መንገዶች፣ ግድቦች፣ የሀይል ማመንጫ እና ማከፋፈያ አውታሮች፣ የትራንስፖርትና መገናኛ አውታሮች እንደ ምሳሌ ይጠቀሳሉ፡፡
2. በተሻለ ጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎት ለመስጠት ይቻል ዘንድ በአንድ አምራች ወይም አቅራቢ ቢሰሩ የተሻለ ውጤት ሊያመጡ በሚችሉ የአገልግሎት ዘርፎች መንግስት በብቸኝነት (Public Monopoly) ወይም ከግል ዘርፉ ጋር በጋራ ሊሰራ ይችላል፡፡

## 2.2 ግብርናና ገጠር ልማት

የግብርናው ዘርፍ ለሀገራችን ኢኮኖሚ ያለው አስተዋጾ ከፍተኛ ሲሆን ለሀገራችን አጠቃላይ ብሄራዊ ምርት (GDP) 35 ከመቶ በላይ እንዲሁም ለሀገሪቱ ህዝብ 70 ከመቶ በላይ የስራ እድል ፈጥሯል፡፡ ሀገራችን ወደ ውጭ ከምትልካቸው እቃዎች ከፍተኛው የግብርና ውጤቶች ሲሆኑ ዋናው የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ይሁን እንጂ ዘርፉ ካለው ሀገራዊ ፋይዳ አንፃር ለግብርናው ዘርፍ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ ነው፡፡ ከግማሽ በላይ የሚሆነው የሀገራችን ህዝብ በገጠር የሚኖር ሲሆን የገጠሩ የሀገራችን ክፍል ዝቅተኛ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች እና ደካማ የመሰረ-ልማት አቅርቦት እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚና የገጠሩ የሀገራችን ክፍል ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት **ነእፓ** ከፍተኛ የፖሊሲ ትኩረት በመስጠት ከግብርናው ዘርፍና ከገጠር ልማት ጋር በተያያዘ የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች አስቀምጧል፡፡

**ግብርና**

1. የሀገራችን የግብርና ዘርፍ ካለበት ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ እና የዝናብ ጥገኝነት ተላቆ ወደ ተሻሻለ እና ሜካናይዝድ ግብርና እንዲቀየር ይደረጋል፣
2. በመስኖ ላይ የተመሰረተ የእርሻ ስራ እንዲስፋፋ ለማድረግ ማበረታቻና ድጋፍ ይደረጋል፣
3. የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ለኢንዱስትሪና አገልግሎት ሰጪ ዘርፍ በቂ ግብዓት እንዲያቀርብና ለኢዱስትሪ ልማት ሰፊ ገበያ እንዲፈጥር የግብርናና የኢንዱስትሪ ሴክተሮች እንዲቀናጁ ይደረጋል፣
4. የሀገራችን ኢኮኖሚ አሁን ካለበት የግብርና-መር ኢኮኖሚ በሂደት ወደ ኢንዱስትሪ-መር እንዲሸጋገር የሚያስችል መዋቅራዊ ሽግግር ይደረጋል፣
5. የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚው ለሀገር ውስጥ ፍጆታ በቂ ምግብ ማምረት እና ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንዲችል ይደረጋል፣
6. በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች እስከ አሁን ድረስ ለእርሻና ለሌሎች የግብርና ስራዎች ያልዋሉ ለም መሬቶች ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ይደረጋል፣
7. ቡና፣ አበባ፣ ጥራጥሬ፣ ቆዳን ጨምሮ ለሀገራችን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኙ የግብርና ምርቶች ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ ይደረጋል፣
8. ዘመናዊ የምርት መሳሪያዎችና የግብርና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሀገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ከፍ እንዲል ይደረጋል፣
9. ዘመናዊ የግብዓትና የምርት አቅርቦት ስርአትን በመገንባት የገበሬውን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነት ማሳደግ፣
10. የሀገራችን ግብርና ዘርፍ ያለበትን የድህረ ምርት (Post harvest) ብክነት በመቀነስ የግብርና ምርትን ለማሳደግ የሚያስችሉ አሰራሮች ተግባራዊ ማድረግ፣
11. ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ውጤቶች እና ጥሬ እቃዎች በሀገር ውስጥ እሴት ተጨምሮባቸው በተሻለ ዋጋ እና ጥራት ለውጭ ገበያ እንዲቀርቡ በማድረግ ሀገራችን ከዘርፉ የምታገኘው የውጭ ምንዛሬ እንዲያድግ ይደረጋል፣
12. የግብርና ምርት እንዲቀንስ የሚያደርጉ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመቀነስ የሚያስችሉ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ዘዴዎችና የተሻሻሉ የግብርና ግብዓቶች ስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፣
13. የግብርና-ኢንዱስትሪን (Agro-Industry) በማስፋፋት ገበሬው ምርቱን ለሀገር ውስጥ ፍጆታና ለውጭ ገበያ ማቅረብ የሚችልበት የገበያ ስርዓት ይዘረጋል፣
14. የግብርናውን ዘርፍ አጠቃላይና ዝርዝር መረጃ በትክክል መሰብሰብ የሚያስችል የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት ዘርፉ ያለበትን ደረጃ በየጊዜው ለማወቅና በመረጃ ላይ የተመሰረተ ፖሊሲ መቅረጽ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣
15. ገበሬዎች ብድርና ሌሎች የግብርና ግብዓቶችን በቀላሉ የሚያገኙበት ስርዓት ተቀርጾ ተግባራዊ ይሆናል፣
16. መሰረታዊ የምግብ አቅርቦትን በሀገር ውስጥ እንዲሸፈን በማድረግ ከውጭ ሀገር የሚደረግ የምግብ ግዥ እንዲቀንስ ብሎም እንዲቆም ይደረጋል፣
17. በተወሰኑ የእህል እና የጥራጥሬ ዓይነቶች የተወሰነውን የአመጋገብ ባህል በመለወጥ በሀገራችን ውስጥ በቀላሉና በብዛት የሚመረቱ የእህል እና የሰብል ዓይነቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፣
18. ሰው ሰራሽ ማዳበሪያን በተፈጥሮ ማዳበሪያ በመቀየር በአካባቢ እና በሰዎች ጤና ላይ የሚደርስን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል የተቀናጀ የግብርና፣ የምርምርና የግብይት ስርዓት ይዘረጋል፣
19. የእንስሳትን ጤና በመንከባከብ የእንስሳት ምርትና የምርት ተዋፅዖ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ ገበሬው ከእንስሳቱ የሚያገኘው ጥቅምና ገቢ እንዲያድግ ስልት ይቀየሳል፣
20. ሰፋፊ/ትልልቅ የንግድ እርሻዎች /Large Scale Commercial Farming/ እንዲስፋፉና እንዲበረታቱ ይደረጋል፣

21. የግብርናው ዘርፍ ዕድገት ለስራ ፈጠራና ለድህነት ቅነሳ ጉልህ ሚና እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

**የገጠር ልማት**

ከሀገራችን ህዝብ አብዛኛው በገጠር የሚኖር ሲሆን፣ የገጠሩ የሀገራችን ክፍል ከከተሞች ጋር ሲነጻጸር በልማትና በአገልግሎት አሰጣጥ እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሰት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በዚህም ምክንያት በከተሞች አካባቢ ከፍተኛ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮች ተፈጥረዋል፡፡ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት፣

1. በጥናት ላይ የተመሰረቱ የተቀናጀ የገጠር ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
2. መልከዓ-ምድራዊና ስነ-ምህዳርን ታሳቢ ያደረጉ የገጠር ኢንዱስትሪ ማስፋፊያ ፕሮግራሞች ተቀርጸው በስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፣
3. ትምህርት፣ ጤና፣ መብራት፣ የንጹህ መጠጥ ውሀ አቅርቦት፣ የስልክ አገልግሎት የመሳሰሉ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች በገጠር አካባቢ በጥራትና በብዛት እንዲቀርቡ ይደረጋል፣
4. አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ግድቦችን በመገንባት ገበሬው የመስኖ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል፣
5. የገጠሩን ኢኮኖሚ ምርታማነት ለማሳደግ የሚረዱ የገጠር የስልጠና ማዕከላትን የማስፋፋት ስራ በስፋት ይሰራል፣
6. በገጠሩ አካባቢ አነስተኛና ወጪ ቆጣቢ ቤቶች በመገንባት የህብረተሰቡ ኑሮ እንዲሻሻል ይደረጋል፣
7. ለገጠሩ ህብረተሰብ የስራ ዕድል በመፍጠር ድህነትን የሚቀንሱ ፕሮጀክቶች በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ተግባራዊ ይሆናሉ፣
8. መንገድን ጨምሮ ሌሎች የገጠር መሰረተ-ልማቶችን በማስፋፋት ምርታማነትን የሚያሳድጉ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ይቀየሳሉ፤ የገጠር ቀበሌዎችን እርስ በርስና ከከተሞች ጋር የሚያገናኙ የገጠር መንገዶች እንዲገነቡ ይደረጋል፣

## 2.3 የአርብቶ-አደር ልማት

ከሀገራችን የቆዳ ስፋት ከግማሽ በላይ የሚሆነው ክፍል የአርብቶ አደር ማህበረሰቦች የሚኖሩበት አካባቢ እንደሆነ ይገመታል፡፡ በአብዛኛው በጠረፋማና ቆላማ የሀገራችን ክፍሎች የሚኖሩት አርብቶ አደሮች እጅግ አስከፊ በሆኑ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አስተዳደራዊ ተግዳሮቶች ውስጥ በቂ የመንግስት ትኩረት ሳያገኙ ረዥም ዘመን አልፏል፡፡ ቢያንስ ለአለፈው ግማሽ ምዕተ ዓመት በሀገሪቱ የተፈራረቁ ስርአቶች የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ እና የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ልማት ትኩረት በመንሳት ህዝቡ በድህነት አዙሪት ውስጥ እንዲማቅቅ አድርገዋል፡፡ ከአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ህይወትና እና ደህንነት ይልቅ ለእንስሳቱ፣ ለሰፋፊና ለም የእርሻ መሬቱ እንዲሁም ሌሎች የከርሰ ምድር ሀብቶቹ ቅድሚያ ሲሰጡ የቆዩት የሀገራችን መሪዎች ከሌሎች የሀገራችን ህዝቦች በከፋ ሁኔታ የአርብቶ አደሩን ህብረተሰብ በልማት ወደ ኋላ እንዲቀር ከፍተኛ በደል ፈጽመውበታል፡፡

የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ካሉበት ዘርፈ ብዙ የህይወት ውጣውረዶች የሚታደገው ልዩ የመንግስት ድጋፍ እና የፖሊሲ አማራጮች በእጅጉ የሚሻ ቢሆንም፣ ዛሬም ድረስ በሀገራችን ፖለቲካ በቂ ትኩረት አላገኘም፡፡ የአርብቶ አደሩን የህብረተሰብ ክፍል ካሉበት ተደራራቢ ችግሮች ለማላቀቅ፣ በሀገራችን ሁለንተናዊ ልማት ውስጥ በቂ ተሳትፎ እና ከልማቷም ፍትሀዊ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማስቻል **ነእፓ** የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል፡፡

1. አርብቶ-አደሩ ማህበረሰብ ከተንቀሳቃሽ የኑሮ ዘይቤ ተላቆ ህይወቱን በተረጋጋ መንገድ መምራት የሚያስችለው የልማት ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይሆናሉ፣

2. አርብቶ-አደሩ ማህበረሰብ የተረጋጋ ኑሮ እንዲመሰርት የሚያስችሉት አነስተኛ መንደሮች ይገነባሉ፡፡ መንደሮቹ የተሟላ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ይኖራቸዋል፣
3. የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ይበልጥ ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችል የተቀናጁ የአርብቶ-አደር ልማት መርሀ-ግብሮች ተግባራዊ ይደረጋሉ፤ የልማት መርሀ-ግብሮቹ በዋናነት ውሀን ማዕከል ያደረጉ ይሆናል፣
4. አርብቶ-አደሩ ማህበረሰብ የአካባቢውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች መምራት ይችል ዘንድ የተጠናከረና ሁሉን አቀፍ የአቅም ግንባታ ስራ ይሰራል፣
5. የአርብቶ አደር ስልተ-ምርት በሀገሪቱ ህጎች በቂ እውቅና እንዲያገኝ፣ ለአርሶ አደርና ሌሎች ስልተ-ምርቶች የሚሰጠው ትኩረት እና የሚደረገው መንግስታዊ ድጋፍ ለአርብቶ አደሩም እንዲሰጥ የሚያደርጉ የህግ ማእቀፎች ይሰናዳሉ፣
6. የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ኑሮ ከእንስሳቱ ህይወት እና ደህንነት ጋር እጅግ የተቆራኘ በመሆኑ ጥራት ያለው የእንስሳት እንክብካቤና የጤና አገልግሎት በመዘርጋት አርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ብሎም አጠቃላይ ሀገራችንን ከእንስሳት ሀብታችን ይበልጥ ተጠቃሚ የሚያደርግ ስርዓት ይዘረጋል፣
7. የአርብቶ አደር አካባቢዎችን መልከዓ-ምድር፣ ስነ-ምህዳርና የአየር ፀባይ ወዘተ ታሳቢ ያደረጉ የልማት ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ለመንደፍ እና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ ጥናቶች እና ምርምሮች ይደረጋሉ፤ በዘርፉ የተሳኩ ዓለም ዓቀፍ ተሞክሮዎችን ለመቅሰምና ጥቅም ላይ ለማዋል ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፣
8. በአብዛኛው በቆላማ እና ጠረፋማ አካባቢ የሚኖረው አርብቶ-አደር ህዝባችን ከሌላው የሀገራችን ህዝብ ጋር ያለው የባህል እና የኢኮኖሚ ትስስር እንዲጠናከር የሚያስችሉ ፕሮግራሞች ተቀርጸው ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
9. የአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ አባላት ከቦታ ቦታ ተንቀሳቃሽ ከመሆናቸው አንጻር ከሌሎች አርብቶ አደር ማህበረሰብ አባላት እና በአዋሳኝ ከሚገኙ አርሶ አደር ማህበረሰብ ጋር ለግጭት ስለሚዳረጉ ህይወታቸው ለአደጋ የተጋለጠ ነው፡፡ ይህንን የአርብቶ አደሩን የደህንነት ስጋት በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራሉ፣
10. የአርብቶ አደሩን ማህበረሰብ ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥና የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ልማትና ብልፅግና ለማፋጠን ልዩ የበጀት ድጋፍ የሚደረግበት አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### 2.4 የመሬት ይዞታ

የመሬት ይዞታና የባለቤትነት ጥያቄ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ቁልፍ እና መሰረታዊ ጥያቄ ሆኖ ለረዥም ዘመናት የቆየ ቢሆንም የህዝብን ፍላጎት በተገቢው መንገድ ያገናዘበ፣ የሀገርን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ልማት በሚያፋጥን መልኩ መልስ ሳያገኝ ቆይቷል፡፡ የመሬት ይዞታና ባለቤትነት ጉዳይ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ የስነ-ህዝብ፣ አካባቢ ጥበቃ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የሚመለከት ዘርፈ ብዙ የፖሊሲ አጀንዳ ነው፡፡

ከዚህ የተነሳ መሬትን አስመልክቶ የሚቀረጹ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ከፍተኛ የንድፈ ሀሳብ እና ዓለም-ዓቀፍ የተግባር ተሞክሮን ያገናዘቡ ሊሆኑ እንደሚገባ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** በፅኑ ያምናል፡፡ የመሬት ይዞታና ባለቤትነት ጥያቄ ለሀገራችን ሁለንተናዊ ብልጽግናና ልማት ያለውን ከፍተኛ ሚና ታሳቢ በማድረግና የመሬት ጥያቄ በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ የነበረውን ከፍተኛ ቦታ ከግምት ውስጥ በማገባት **ነእፓ** መሬትን አስመልክቶ የሚከተሉትን ፕሮግራሞች ይከተላል፡፡

1. በገጠርም ይሁን በከተማ የሚገኝ መሬት የመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ንብረት ሲሆን መሬትን የማስተዳደር ኃላፊነት የመንግስት ይሆናል፣

2. በገጠር ለእርሻ አገልግሎት የሚውል መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ለአርሶ አደሮች ይሰጣል፣ ገበሬዎች በይዞታቸው ስር በሚገኝ መሬት ላይ ያሏቸው መብቶች እና ጥቅሞች ሳይሸራረፉ ይከበራሉ፣
3. ገበሬዎች በግል ይዞታቸው ስር ያለን መሬት የማከራየት መብት ይኖራቸዋል፤
4. **ነእፓ** የሀገራችንን ሁለንተናዊ የእድገት ደረጃ ታሳቢ ባደረገ ሁኔታ መሬትን በሂደት ሙሉ ለሙሉ መሸጥና መለወጥ የሚቻልበት የፖሊሲ አቅጣጫ ሊከተል ይችላል፤ ይህ አሰራር ከአጠቃላይ ሀገራዊ የምጣኔ ሀብት፣ የፖለቲካ እና ማህበራዊ እድገት ጋር ተገናዝቦ በጥናት የሚወሰን ይሆናል፣
5. የከተማ መሬትን በተመለከተ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት ለመገንባት ለሚጠቀሙበት መሬት የይዞታ ማረጋገጫ ህጋዊ ሰነድ እንዲያገኙ ይደረጋል፣ በይዞታቸው ስር ባለ መሬት ላይ ያሏቸው መብቶችና ጥቅሞች እንዲከበሩ የህግ ዋስትና ይሰጣል፣
6. የአርብቶ አደር አካባቢዎች ለአርብቶ አደሩ እንስሳት ግጦሽ የሚያገለግል መሬት በወል ይዞታ ሊቆይ ይችላል፣
7. በገጠርም ሆነ በከተማ ለልማት ስራዎች ከመሬታቸው ለሚለሱ ዜጎች የክልል መስተዳድሮች ወይም የማዕከላዊ መንግስት ተገቢውን ካሳ በገንዘብ ወይም በአይነት ይከፍላሉ፣
8. ሰፋፊ እና ዘመናዊ እርሻ እና የእንስሳት እርባታ ስራ ላይ ለመሰማራት ለሚሹ የሀገር ውስጥና የውጭ ኢንቨስተሮች መንግስት መሬትን በሊዝ ያከራያል፣
9. የሀገራችን የመሬት ፖሊሲና አስተዳደር ከሀገሪቱ የኢኮኖሚና የማህበራዊ እድገት ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ በመሬት ይዞታ፣ ባለቤትነት እና አስተዳደር ዙሪያ ተከታታይ እና አሳታፊ ጥናቶች ይደረጋሉ፡፡

### 2.5 መሰረተ-ልማት

መሰረተ-ልማት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ልማት የጀርባ አጥንት ነው፡፡ በዓይነትና በብዛት ሰፊ የመሰረተ ልማት መኖር ምርትንና ምርታማነትን ለማሳለጥ፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ንግድን ለማሳደግ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አገልግሎቶችን በቀላሉ ከቦታ ወደ ቦታ ለማንቀሳቀስ የምርት ዋጋን ለማረጋጋት፣ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ወዘተ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው፡፡ በዚህ ፕሮግራም ውስጥ መሰረት ልማት መንገድ፣ የኃይል አቅርቦት፣ ግድቦች፣ የውሃና ፍሳሽ አገልግሎት፣ ትራንስፖርት፣ ቴሌኮሚኒኬሽን፣ የተፈጥሮ ጋዝ ወዘተ የሚያካትት ሲሆን ዘርፉን ለማሳደግና ለልማት ያለውን አስተዋፅዖ ከፍ ለማድረግ የሚከተሉት የፖሊሲ አቅጣጫዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. የትራንስፖርት አገልግሎትን ፈጣንና ቀልጣፋ ለማድረግ የመንገድ፣ የባቡርና እና የአየር ትራንስፖርት መሰረተ ልማት አውታሮች በስፋት ይገነባሉ፣
2. በፍጥነት እያደገ በመሄድ ላይ ካለው የሀገራችን ህዝብ ብዛት አንጻር ተመጣጣኝ የሆነ የመሰረተ ልማት ግንባታ ይዘረጋል፣ በተለይም በከተሞች አካባቢ ያለውን ከፍተኛ የትራንስፖርት ችግር ለመቅረፍ ዘመናዊ እና አማራጭ የትራንስፖርት አገልግሎቶች እንዲገነቡ ይደረጋል፣
3. የግሉ ዘርፍ በመሰረተ ልማት ግንባታ ላይ እንዲሳተፍ ማበረታቻና ድጋፍ ይሰጣል፣
4. በሀገር አቀፍ ደረጃ የመሰረተ ልማት አውታር ስርጭት ፍትሀዊ እንዲሆን ልዩ ትኩረት ይደረጋል፣ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ አዋጭነት ባላቸው የጠረፍ እና ዝቅተኛ (Low land) አካባቢዎች የመሰረተ ልማት አቅርቦትን ለማስፋ ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፣
5. ሀገራችን ያለባትን የሀይል አቅርቦት እጥረት ለመቀነስና በቂ እና አስተማማኝ የሀይል አቅርቦት በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ የተፈጥሮ ጋዝ አቅርቦት እንዲጨምር ይደረጋል፣

6. ከጎረቤት ሀገሮች እና ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ጋር ያለውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ትስስሮችን ለማጠናከር ሀገር አቋራጭ የትራንስፖርት፣ የኃይል፣ የቴሌኮም ወዘተ አውታሮች ከጎረቤት ሀገሮችና ከሌሎች ዓለም-ዓቀፍ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ይገነባሉ፣
7. ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በመስማማትና በቅንጅት በመስራት ፈጣንና አስተማማኝ የወደብ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት የሚቻልበት አሰራር ይዘረጋል፤ ከሀገራቱ ጋር በመደራደርም ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ ወደብ እንዲኖራት ለማድረግ **ነእፓ** ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል።
8. ፈጣንና ጥራት ያለው የኢንተርኔትና ሌሎች የቴሌኮም አገልግሎቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ ይደረጋል፣ የኢንተርኔት አገልግሎት በመላው የሀገሪቱ ክፍል በጥራት እንዲዳረስ ይሆናል፣
9. የሎጂስቲክ ስርዓቱ እንዲዘምንና በዓለም-አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያስችሉ ፖሊሲዎች ተቀርጸው ተግባራዊ ደረጋሉ፣
10. የሀይል አቅርቦት እጥረትን ለመቀነስና ተደራሽነቱን ለመጨመር አማራጭ የኃይል ምንጮች (off gride) ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፣ ታዳሽ ሀይል ትኩረት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፣፣
11. ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ተማጣጣኝ የሀይል አቅርቦት ይኖር ዘንድ በሀገር ውስጥ የነዳጅ ፍለጋና የማልማት ስራ ይሰራል፣ የነዳጅ ክምችት ይኖርባቸዋል ተብለው በሚገመቱ አካባቢዎች የተጠናከረ የፍለጋ ስራ ይሰራል፣
12. በከፍተኛ መዋዕለ-ንዋይ የተገነቡ የመሰረተ ልማት አውታሮች የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት በጥራት ይሰጡ ዘንድ ተገቢ ጥገናና እንክብካቤ እንዲያገኙ ይደረጋል፣ ዘመናዊና ቀልጣፋ የመሰረተ ልማት አስተዳደር ስርአት ይዘረጋል፡፡

### 2.6 ንግድ እና ኢንቨስትመንት

የሀገር ውስጥ እና የውጭ ንግድ ለአንድ ሀገር ልማት ያለው ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ቀልጣፋ፣ ቀላል እና የተቀናጀ የንግድና ኢንቨስትመንት ስርዓት ለሀገራችን ኢኮኖሚ ዕድገትና ለዜጎች ኑሮ መሻሻል ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የግብርና እና አምራች ኢንዱስትሪን በማሳለጥና በማቀናጀት ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገትን ለማሳካት የሀገር ውስጥና የውጭ ንግድን ማዘመንና ጠንካራ የፖሊሲ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ፈጣንና ዘላቂ ልማት፣ የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ እና የፊስካል ፖሊሲ፣ በቂ የካፒታል ፍሰት፣ ሁነኛ የሀብት አጠቃቀም፣ ቀልጣፋ የንግድና የኢንቨስትመንት አካባቢ ይፈልጋሉ፡፡ ከዚህ አንጻር **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የሚከተሉትን የንግድና የኢንቨስትመንት ፕሮግራሞች ተግባራዊ ለማድረግ ይሰራል፡፡

1. የንግድና የኢንቨስትመንት ህጎች ከሌሎች የልማት ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር እንዲቀናጁና እና እንዲተሳሰሩ ይደረጋል፣
2. የሀገራችን የንግድ ህጎች ከአዓለም-ዓቀፍ የንግድ ስርዓት እና የአሰራር ደንቦች ጋር በሚጣጣም፣ ዓለም-ዓቀፍ ተወዳዳሪነትን በሚያረጋግጥ እና ሃገራችንን የተሻለ ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ ይሻሻላሉ፣
3. ሀገራችን ውስጥ በተለያዩ የስራ መስኮች ለመሰማራት ለሚፈልጉ የውጭ ባለሀብቶች በአጭር ጊዜ እና በተቀላጠፈ መንገድ የኢንቨስትመንት ስራቸውን መጀመር እና ማካሄድ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣
4. ከጎረቤት ሀገሮችና ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ጋር ያለንን የሸቀጥና የአገልግሎት ንግድ ትስስር ከፍ ለማድረግ ስር-ነቀል የፖሊሲ ማሻሻያ ስራ ይሰራል፣
5. በአብዛኛው የግብርና ምርቶችን በመላክ ላይ የተመሰረተው የሀገራችን የውጭ ንግድ ሌሎች የኢንዱስትሪ ምርቶችን እንዲያካትት በማድረግ (Product Diversification) በግብርናና ጥሬ እቃዎች ዋጋ መዋዠቅ በሀገራችን ኢኮኖሚ ላይ የሚደርሰው ቀውስ እንዲቀንስ ይደረጋል፣

6. ከውጭ የምናስመጣቸውን ምርቶች በመቀነስና ወደ ውጭ የምንልካቸውን በመጨመር የሀገራችን የውጭ ምንዛሬ እጥረት ለመቀነስ ብሎም የተረጋጋ የውጭ ምንዛሬና የንግድ ሚዛን እንዲኖር የሚያደርጉ አሰራሮችና ፖሊሲዎች ተቀርጸው ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
7. የተመጣጠነ የውጭ ንግድ ስርዓት ለመፍጠር የሚረዱ የንግድና የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
8. የሀገራችን ምርቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል የንግድ፣ የኢንቨስትመንት፣ የቀረጥና የካፒታል ፍሰት ስርአት ይዘረጋል፣
9. ሀገራችን የዓለም የንግድ ድርጅት አባል ትሆን ዘንድ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ከድርጅቱና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ድርድር ይካሄዳል፣
10. ኢትጵያውያን ባለሀብቶችና የውጭ ኢንቨስተሮች በንግድና ኢንቨስትመንት ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ዝግጅት ላይ በበቂ ሁኔታ እንዲሳተፉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፣
11. የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (FDI) ለመሳብ የሚያስችል ምቹ የንግድና የኢንቨስትመንት ስርዓት ይዘረጋል፣
12. ውጤታማ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ የሀገራችን ባለሀብቶች ከውጭ ባለሀብቶች ጋር በሽርክና የሚሰሩበት አሰራር እንዲጠናከር አስፈላጊው የህግ እና የፖሊሲ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

## 2.7 ቱሪዝም

ቱሪዝም በብዙ ሀገራት ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየሰፋ የመጣ የኢኮኖሚ ዘርፍ ነው:: ቱሪዝም ለአንድ ሀገር ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከማመንጨት በተጨማሪ የስራ ዕድሎችን በመፍጠር፣ ድህነትን በመቀነስና ዘላቂ ልማትን በማፋጠን ረገድ ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል። ሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ሰው ሰራሽና ባህላዊ ቅርሶች ያሏት ሀገር ናት። ሆኖም ሀገራችን ኢትዮጵያ ካላት እምቅ የቱሪዝም ሀብት በተለያዩ ማነቆዎች ምክንያት ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ሳታገኝ ቆይታለች። ቱሪዝም ያለውን ኢኮኖሚያዊ ፋይዳና በዘርፉ ውስጥ የሚታዩ ማነቆዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት **ነእፓ** ለቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የሚከተሉትን ፕሮግራሞች ተግባራዊ ለማድረግ ይሰራል።

1. ሀገራችን ኢትዮጵያ ያሏትን ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ሰው ሰራሽና ባህላዊ የቱሪስት መስህቦች መጠበቅና መንከባከብ፤
2. አሁን ካሉት ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ሰው ሰራሽና ባህላዊ መዳረሻዎች በተጨማሪ የመዝናኛ ቱሪዝም፣ የኮንፈረንስ ቱሪዝም፣ የትምህርት ቱሪዝም፣ የህክምና እንዲሁም ሌሎች አዳዲስ የቱሪስት መስህቦችን የማበልፀግ ስራ ይሰራል፣
3. ጥራት ያለው አገልግሎት የሚሰጡ ሆቴሎችንና የመዝናኛ ተቋማትን፣ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችን ማካሄድ የሚያስችሉ ሁለገብ አዳራሾችን፣ የህክምና አገልግሎት ተቋማትን፣ የመጓጓዣና የመገናኛ አውታሮችንና ሌሎች የመሰረተ ልማቶችን አቅርቦት ለማስፋት እና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራሉ፣
4. አስተማማኝ ሰላምና ፀጥታ በማስፈንና የቱሪስቶችን ሰላምና ደህንነት በመጠበቅ ለቱሪስቶች ምቹ ከባቢ እንዲፈጠር የተቀናጀ ስራ ይሰራል፣
5. ሀገራችን በዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ያላትን አሉታዊ ስም (ድርቅ፣ ረሀብ፣ ግጭት፣ ወዘተ) በመቀየር በምትኩ የሀገራችንን አዎንታዊ ገፅታ የሚያሳዩ፣ ብርቅና ድንቅ የቱሪስት መዳረሻዎችን አጉልተው ማሳየት የሚችሉና ዓለም ዓቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ የማስታወቂያና የህዝብ ግንኙነት ስራዎች ይሰራሉ፣
6. በቱሪዝም መስክ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እንዲያድግ የተለያዩ ማበረታቻዎችና ድጋፎችን ይሰጣሉ፣
7. በዘርፉ የሚታየውን የሰለጠነ የሰው ኃይልና የቴክኖሎጂ እጥረት በመቅረፍ ጠንካራ የቱሪዝም ስርዓት ይዘረጋል፣
8. በቱሪስት መዳረሻዎች አካባቢ የሚኖሩ ዜጎች ከዘርፉ ቀጥተኛ ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስርዓት በመፍጠር ዜጎች ለቱሪዝም ዘርፉ እድገት በንቃት እንዲሳተፉ እና ባለድርሻ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

## 2.8 አምራች ኢንዱስትሪ

የሀገራችን አምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የስራ ዕድል ከመፍጠር አኳያ እና የውጭ ምንዛሬን ከመፍጠር አንጻር ያለው ሚና ዝቅተኛ ሲሆን ይህም ዘርፉ ለጠቅላላው ኢኮኖሚ ያለው አስተዋጾ እጅግ አነስተኛ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ዘርፉ ኋላ ቀር ቴክኖሎጂ የሚጠቀም ሲሆን ምርታማነቱ ዝቅተኛ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ የሀገራችን የኢንዱስትሪ ምርቶች በዓይነትም በብዛትም ትንሽ ናቸው፡፡ **ነእፓ** በሀገራችን የማምረቻ ኢንዱስትሪዎችን ለማስፋፋት የሚከተሉትን ፕሮግራሞች ይከውናል፡፡

1. ዘርፉን አሁን ካለበት ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር የግል ባለሀብቶች በከፍተኛ ደረጃ ተሳታፊ የሚሆንበት ሁኔታ ላይ ትኩረት ይሰጣል፣
2. የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ፍትሀዊ በሆነ መንገድ እንዲስፋፉ ይደረጋል፣
3. ለማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ዕድገት የሚያግዙ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማቶች እንዲስፋፉና በየደረጃው ያሉ የመንግስት ተቋማት ለዘርፉ እድገት ድጋፍ የሚያደርጉበት አሰራር ይዘረጋል፣
4. አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት፣ የትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን አውታሮች ወዘተ ከኢንዱስትሪ ልማት ጋር ተቀናጅተው እንዲሰሩ ይደረጋል፣
5. የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች በሀገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን የስራ አጥነት ችግር ለመቅረፍ ከተለያዩ ተቋማት ለሚመረቁ ወጣቶች የስራ ዕድል መፍጠር እንዲችሉ የተቀናጀ ስራ ይሰራል፣
6. የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ከግብርናው ዘርፍ ጋር በገበያና በግብዓት አቅርቦት ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ እንዲሆኑ በማድረግ የሀገር ውስጥ ምርት በጥራትና በበቂ ሁኔታ እንዲመረት ማድረግና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመተካት የውጭ ምንዛሬን መቆጠብና የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ የሚቻልበት ፖሊሲ እና አሰራር ይዘረጋል፣
7. የተለያዩ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለማምረት የሚያስፈልጉ የማምረቻ ማሽነሪዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ማድረግና በቀላሉ በሀገር ውስጥ የማይመረቱትን በአጭር ጊዜና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡበት ሁኔታ ይመቻቻል፣
8. በሀገሪቱ ያሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከላት የኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚፈልገውን የሰው ኃይል በማሰልጠንና የቴክኖሎጂ አማራጮችን በማቅረብ የኢንዱስትሪው ዘርፍ የአቅም ግንባታ ስራ እንዲሰሩ ይደረጋል፣
9. በስራ ላይ ያሉ ኢንዱስትሪዎች ያሉባቸውን ችግሮች በመለየትና አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ምርታማነታቸው እንዲያድግ የሚያስችል አሰራር ይቀየሳል፣
10. ሀገር በቀል የዕደ-ጥበብ ስራዎች እንዲስፋፉና ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ያላቸው አስተዋፅዖ ከፍ እንዲል ልዩ ድጋፍ ይደረጋል፣
11. ቀጣይነት ያለው የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ዕድገት እውን እንዲሆን ለማድረግ ኢንዱስትሪዎች በማህበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ላይ ያላቸው ተጽዕኖ ቀድሞ መለየት የሚያስችል ዘመናዊ የኢንዱስትሪ አስተዳደርና ቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት ኢንዱስትሪዎች በአካባቢና በዜጎች ማህበራዊ ህይወት ላይ ሊፈጥሩ የሚችሉትን አሉታዊ ተጽዕኖ የሚቀንስ አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፣
12. የኢንዱስትሪ ሴክተሩን የሚያበረታታ በጥናት ላይ የተመሰረተ የታክስና የቀረጥ ፖሊሲ ተግባራዊ ደረጋል፣
13. በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች፣ የክልሎቹን የተፈጥሮ ሀብት አቅምና ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት ዘመናዊ የኢንዱስትሪ መንደሮች እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

## 2.9 ማክሮ ኢኮኖሚ ፕሮግራሞች

### 2.9.1 የገንዘብ እና ፊስካል ፖሊሲ

የገንዘብ ፖሊሲ (Monitary Policy) የአንድን ሀገር አጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለመምራትና ለመቆጣጠር ብሎም በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖር የገንዘብ መጠንና ፍሰትን ለመወሰን የሚያገለግል የፖሊሲ መሳሪያ ነው፡፡ የገንዘብ ፖሊሲ መሰረታዊ ዓላማ የሀገር ውስጥ አጠቃላይ የምርት እድገትን፣ የዋጋ ግሽበትን፣ የስራ እድል ፈጠራን፣ እና የውጭ ምንዛሬን ሁነኛና የተሻለ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ በየጊዜው የሚዋዥቀውን የሀገራችን ማክሮ-ኢኮኖሚ ለማረጋጋት በመረጃ ላይ የተመሰረተ የገንዘብ ፖሊሲ መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የሚከተሉትን የገንዘብ ፖሊሲ ዓላማዎች እውን ለማድረግ ይሰራል፡፡

1. የገንዘብ ፍሰትን በመቆጣጠር የሀገራችን ገንዘብ (ብር) የመግዛት አቅሙ የተረጋጋ እንዲሆን ሳይንሳዊ እና በጥናት የተደገፉ ርምጃዎች ይወሰዳሉ፣
2. በገበያ የሚመራና አስፈላጊም ሲሆን የመንግስት ቁጥጥር የሚደረግበት የውጭ ምንዛሬ ግብይት ስርዓት በመዘርጋት የውጭ ምንዛሬ የተረጋጋ እንዲሆን ይደረጋል፣
3. የካፒታል ፍሰትን ከሀገር ኢኮኖሚ ልማት ጋር የተጣጣመ በማድረግ የተረጋጋ የዋጋ መጠን እና የውጭ ምንዛሬ እንዲፈጠር ይደረጋል፣
4. የሀገር ውስጥ የቁጠባ አቅምን በማሳደግ ለልማት የሚውል በቂ የካፒታል አቅርቦት እንዲኖር ማድረግ፣
5. የኢኮኖሚ መቀዛቀዝንና ድብርትን (Recession and depression) ለመከላከል የሚረዱ የገንዘብ ፖሊሲ ርምጃዎች ይወሰዳሉ፣
6. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክን ሁለንተናዊ አቅም በማጠናከር በሀገሪቱ ጤናማ የገንዘብ ፖሊሲ እና የገንዘብ አስተዳደር ስርአት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

### 2.9.2 የመንግስት በጀት እና እዳ

የአንድን ሀገር የማክሮ-ኢኮኖሚ እድገት እና ይዘት ከሚወስኑት ነገሮች መካከል የመንግስት በጀትና ብድር ዋነኛዎቹ ናቸው፡፡ የተመጣጠነ የመንግስት ገቢ እና ወጪ የተረጋጋ ኢኮኖሚ እንዲኖር ከፍተኛ ሚና ይጫዋታል፡፡ ከፍተኛ የዋጋ ንረትን ከሚፈጥሩ ጉዳዮች መካከል ገቢን ያላገናዘበ ከፍተኛ የመንግስት ወጪና ብድር ናቸው፡፡ ለአጭር ጊዜ የፖለቲካ ጥቅም ሲባል በርካታ ፕሮጀክቶችን ለመገንባት መንግስት ከሀገር ውስጥና ከውጭ ባንኮች፣ ከዓለም ዓቀፍ አበዳሪ ድርጅቶችና ከሌሎች አካላት የሚበደረው ገንዘብ ኢኮኖሚው እንዳይረጋጋ ከፍተኛ ጫና ይፈጥራል፡፡ በእዳ የሚገኝ ገንዘብ የረዥም ጊዜ ጥቅም በሌላቸው እና በሚገባ ባልተጠኑ ፕሮጀክቶች ላይ ሲውል ምጣኔ ሀብታዊ ጉዳቱ ድርብርብ ይሆናል፡፡ ያልተመጣጠነ የመንግስት በጀትና እዳ ለሀገራችን ኢኮኖሚ አለመረጋጋት ከፍተኛ ምክንያቶች ናቸው፡፡ ከመንግስት በጀት እና እዳ ጋር በተያያዘ ያሉ ችግሮችን በዘላቂነት ለመቅረፍና የተረጋጋ የማክሮ-ኢኮኖሚ ለመፍጠር የሚከተሉት ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. የመንግስት ጠቅላላ ወጪ ከገቢ ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን የሚያስገድድ የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት የመንግስት ወጪ ከተለያዩ ምንጮች ከሚሰበስበው የመንግስት ገቢ ጋር እኩል ወይም ተቀራራቢ እንዲሆን ይደረጋል፣
2. የመንግስት የበጀት ጉድለት ከጠቅላላ ሀገራዊ ምርት ያለው ምጣኔ ወይም መጠነ-ጉድለት (Budget deficit/GDP ratio) ለጤናማ ኢኮኖሚ ከሚያስፈልገው ደረጃ እንዳያልፍ የቁጥጥር ስርአት ይዘረጋል፣
3. የሀገሪቱ የብድር ጫና ከጠቅላላ ሀገራዊ ምርት ያለው ምጣኔ ወይም መጠነ-ብድር (Debt/GDP ratio) በህግ እንዲወሰን በማድረግ መንግስት ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ የመበደር ስልጣኑ እንዲገደብ የህግ ማዕቀፍ ይበጃል፣

4. የመንግስት የበጀት ስርዓትን በማጠናከር ዘላቂ ልማታችንን የሚያውክ እና ለከፍተኛ የወለድ ክፍያ የሚዳርግ ብድርን ለመከላከል የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፣
5. የመንግስትን ገቢ ለማሳደግ ተከታታይ፣ ሳይንሳዊና በጥናት ላይ የተመሰረተ የታክስ ማሻሻያ ፕሮግራም ይካሄዳል፣ የግብር ዓይነቶችና መጠን እንዲሻሻሉ ይደረጋል፣
6. ሁለቱን የማክሮ-ኢኮኖሚ ተግዳሮቶችን፣ ማለትም የዋጋ ግሽበትና ስራ አጥነት፣ በማመጣጠን የተረጋጋ የማክሮ-ኢኮኖሚ አውድ ለመፍጠር የሚረዱ የተቀናጀ የገንዘብ እና የፊስካል ፖሊሲ ስርአቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

**2.9.3 የፋይናንስ ተቋማት**

ፋይናንስና የፋይናንስ ተቋማት የሀገራችንን ኢኮኖሚ በማሳደግ ያላቸውን ከፍተኛ ሚና እና ድርሻ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የፋይናንስ ስርዓትና ተቋማት እንዲገነቡ ጥረት ይደረጋል፡፡ ቀልጣፋና ዘመናዊ የፋይናንስ ስርዓት ለንግድና ኢንቨስትመንት መስፋፋት፣ ለስራ ዕድል መፈጠር፣ ለተረጋጋ ምጣኔ ሀብታዊ እድገት፣ ለድህነት ቅነሳ፣ ለዘላቂ ልማት ወዘተ የማይተካ ሚና አለው፡፡ የሀገራችን የፋይናንስ ተቋማት ብዛትና አሰራር ዝቅተኛ ሲሆን ለብሄራዊ የምጣኔ ሀብት ዕድገት ያለው አስተዋፅዖም ዝቅተኛ ነው፡፡ ዘርፉ ያለበትን ውስብስብ ችግሮች ለመቅረፍና ለልማት ያለውን አስተዋፅዖ ከፍ ለማድረግ የሚከተሉት ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. የፋይናንስ ተቋማት የብድር አሰጣጥ ስርዓት ዘላቂ ልማትን፣ የተመጣጠነ ክልላዊ ዕድገትን፣ የስራ ዕድል ፈጠራን የሚያግዝ ይሆን ዘንድ የተሻሻሉ የባንክ ስራ አዋጅ እና መመሪያዎች ይዘጋጃሉ፣
2. የፋይናንስ ተቋማት የዜጎችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመፍታት በሚያግዙ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ የሚያበረታታ አሰራር ይቀየሳል፣
3. ከወለድ ነጻ እና አካታች የባንክና የፋይናንስ ስርአት ተግባራዊ ይደረጋል፣
4. ዘመናዊ የፋይናንስ ተቋማትን በብቃት የሚመሩና የሚያስተዳድሩ የፋይናንስ ባለሙያዎችን ማፍራት የሚችሉ የማሰልጠኛ ተቋማት እንዲስፋፉ ድጋፍ ይደረጋል፣
5. የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ለድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች ጉልህ አስተዋጾ ማድረግ የሚችሉበት አግባብ እንዲፈጠር ቀልጣፋ እና አዋጭ አሰራሮች ይቀየሳሉ፣
6. የገጠር የፋይናንስ ተቋማት እንዲስፋፉና እንዲጠናከሩ ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል፣
7. የሞባይልና የኢንተርኔት የባንክ አገልግሎቶችን ጨምሮ ሌሎች አዳዲስ እና ዘመናዊ የፋይናንስ ስርዓቶችን በማስፋፋት የፋይናንስ ተቋማት የሚሰጡት አገልግሎት ፈጣንና ቀልጣፋ እንዲሆን ይደረጋል፣
8. የፋይናንስ ተቋማትና አገልግሎት ስርጭት በሀገር አቀፍ ደረጃ ፍትሀዊ እንዲሆን ይደረጋል፣ የፋይናንስ ተቋማት ተደራሽነት ከፍ እንዲል የሚያደርጉ የህግና አስተዳደራዊ ማሻሻያዎች ይደረጋሉ፡፡

# 3 ማህበራዊ ፕሮግራም

## 3.1 ትምህርት

የሰለጠነ የሰው ኃይል ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገትና ብልጽግና ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች ዋነኛው ነው፡፡ የተማረ የሰው ኃይል ውስን የተፈጥሮ ሀብትን አቀናብሮ ፈጣንና ዘላቂ ልማት፣ የተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓትና አስተማማኝ ሰላም፣ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ወዘተ ለመገንባት የማይተካ ድርሻ አለው፡፡ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ዘርፈ ብዙ እና ውስብስበ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮችና ተግዳሮቶች ላላቸው ሀገሮች፣ ካሉበት የድህነት አዙሪት ለመላቀቅ ትምህርትና ስልጠና ቁልፍ የለውጥ መሳሪያ ናቸው፡፡ የትኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ፤ ግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ አገልግሎት ሰጭ የሰለጠነ እና የበቃ የሰው ኃይል ይሻል፡፡ የተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓት፣ መልካም አስተዳደር፣ ነጻና ግልጽ ምርጫ፣ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር፣ ፖለቲካዊ መቻቻል ወዘተ ስልጡን ማህበረሰብ ይፈልጋሉ፡፡ ሰብአዊ መብቶችን የሚያከብር፣ ለሰው ልጅ ነጻነት፣ ደህንነትና እኩልነት ዘብ የሚቆም፣ ለፍትሕና ለሠላም መከበር የሚታገል፣ በአካልና በሥነ-ምግባር የታነጸ፣ ለሀገርና ለህዝብ ፍቅር ያለው፣ ሁለንተናዊ ስብዕና የተላበሰ ትውልድ የማፍራት ስራ ከትምህርት ቤት ይጀምራል፡፡ በቂ የተማረና የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት በንድፍ ሀሳብና በተሞክሮ የተረጋገጠ፣ የሀገራችንን የትምህርትና ስልጠና ታሪክ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የእድገት ደረጃ፣ የህዝቦቿን ወግ፣ ባህልና ብዝሀነት ወዘተ ከግምት ውስጥ ያስገባ፣ ዓለም ዓቀፍ የስነ-ትምህርት ደረጃዎችንና እመርታዎችን ያገናዘበ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲና ፕሮግራም ያስፈልጋል፡፡

የትምህርት ስርዓታችን በእውቀት የተካኑ፣ በጥልቀት ማስተንተንና መፍጠር የሚችሉ፣ ዘመናዊና ሳይንሳዊ የአመራር ብቃት ያላቸው፣ በመልካም ስነ ምግባር እና ሰብዓዊነት የተሞሉ፣ የሀገር እና ህዝብ ፍቅር ያላቸው፣ ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው እና ለሀገራቸው ዕድገት አስተዋፅዖ የሚያበረክቱ ወጣቶችን ማፍራት እንዲችል ተደርጎ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ በሰው ኃይል ልማት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት በየትኛውም ዘርፍ ላይ ከሚፈስ መዋዕለ-ንዋይ እጅግ አዋጭና ለግለሰብ፣ ማህበረሰብና ለሀገር ዕድገት ተወዳዳሪ የሌለው አስተዋፅዖ ማድረግ የሚችል ነው፡፡ የሀገራችን የትምህርትና ስልጠና ሴክተር በበርካታ ውስብስብ ችግሮችና ተግዳሮቶች የተከበበ ነው፡፡ የሀገራችን የትምህርት ዘርፍ ችግሮች ሲዳሰሱ የትምህርት ስርጭትና ተደራሽነት፣ ጥራት፣ አግባብነትና ፍትሐዊነት ጎልተው ይታያሉ፡፡ እነዚህንና ሌሎች ከትምህርትና ስልጠና እንዲሁም ከሰው ኃይል ልማት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የሚከተሉት ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. የዘመናችንን መልካም አጋጣሚዎች በተሻለ መንገድ ለመጠቀምና እና ተግዳሮቶችን ለመቋቋም የሚችል ትውልድ ማፍራት የሚችል የትምህርት ስርዓት ይዘጋጃል፣ የተማሪዎችን የችግር ፈችነት አቅም ከፍ የሚያደርጉ የትምህርት ፕሮግራሞች ይቀረጻሉ፣
2. የትምህርት ስርዓታችን አህጉራዊና ዓለም-ዓቀፍ ተወዳዳሪነታችንን ከፍ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ይቀረጻል፣
3. ቅድመ መደበኛ፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ፣ የቴክኒክና ሙያ ስርዓት ትምህርትና የማስተማር ዘዴዎች እንዲሻሻሉ ይደረጋል፣
4. የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ተፈትሾ ከሀገራችን ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ጋር በተናበበ መልኩ ይቀረጻል፣
5. የትምህርት ሴክተሩ ቁልፍ ግብዓት ለሆኑት መምህራን ልዩ ትኩረት በመስጠት የመምህርነት ሙያ የተከበረና በህብረተሰቡ ውስጥ የላቀ ሙያ እንዲሆን ለመምህራን ልዩ ልዩ ድጋፎችና ማበረታቻ ይደረጋል፣
6. የሞራል፣ የስነ-ምግባርና ስነ-ዜጋ ትምህርቶች በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ በሚገባ ተዋህደው ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ጀምሮ ለተማሪዎች በተጠናከረ መንገድ እንዲሰጡ ይደረጋል፣

7. ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ሂሳብ (STEM) ትምህርቶች ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ አራቱ የትምህርት ዓይነቶች ዓለም-አቀፍ ተሞክሮን በመዳሰስ በተዋሀደ እና በተቀናጀ መንገድ የሚሰጡበት ስርዓተ-ትምህርት ይቀረጻል፣
8. ዜጎች ቢያንስ የአስር ዓመት አጠቃላይ መሰረታዊ ትምህርት እንዲማሩ የመንግስትና ቤተሰብ ግዴታ ይሆናል፣
9. ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ልዩ ትኩረትና ድጋፍ ይደረጋል፣
10. ትምህርት ቤቶች በቴክኖሎጂ የታገዘ የትምህርት አሰጣጥ አቅም እንዲኖራቸው ለማስቻል የድምጽ እና የምስል ክምችት እንዲኖራቸው፣ የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በቂ ድጋፍ ይሰጣል፣
11. በትምህርት ዘርፍ ለተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ልዩ ልዩ ማበረታቻና ድጋፍ ይደረጋል፣ የመንግስትና የግል የትምህርት ተቋማት የቁጥጥር እና ግምገማ ስርዓት ተመሳሳይ እንዲሆን የሚደረግ ሲሆን፣ በግል የትምህርት ተቋማት ላይ ብቻ ትኩረት እና አላስፈላጊ ጫና የሚፈጥር ብልሹ አሰራር እንዲቀር ይደረጋል፣
12. የትምህርት ተቋማትን ከፖለቲካ ነጻ በማድረግ መምህራንና ተማሪዎች በትምህርታቸው ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋል፡፡ የትምህርት ተቋማት ከመንግስት እና ከህብረተሰቡ ጋር በመረዳዳት ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት ስርዓት ይዘረጋል፣
13. በትምህርት ሽፋንና ጥራት ዝቅተኛ ደረጃ ለሚገኙ የአርብቶ-አደርና ከፊል አርብቶ-አደር አካባቢዎች ልዩ ድጋፍ በማድረግ የሀገራችን የትምህርት ስርጭት ፍትሀዊ እንዲሆን ይደረጋል፣
14. የቅድመ-መደበኛ፣ የመጀመሪያ ደረጃ፣ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና የከፍተኛ ትምህርት ቅበላ፣ ጥራት፣ ሽፋን ከሰሀራ በታች ካሉ ሀገሮች የተሻለ እንዲሆን ይደረጋል፣
15. ተማሪዎች ከመጀመሪያ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንዲሸጋገሩ ድልድይ ሆነው የሚያገለግሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ከፍተኛ እጥረት ለመቀነስ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ግንባታ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፣
16. በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ ከግምት ውስጥ ያስገቡ፣ የጎልማሶችን ምርታማነት ሊያሳድግ የሚችል፣ ከጐልማሶች ሕይወት ጋር በቀጥታ የሚገናኙ እና የጐልማሶችን ፍላጐት መነሻ ያደረጉ የክህሎት ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

**“ትምህርት-ተኮር ብሄራዊ የልማት ስትራቴጂ”**

**የነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ለትምህርትና አጠቃላይ የሰው ኃይል ልማት የሚሰጠው ትኩረት እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ትምህርትና ስልጠና እንደ ሌሎች የልማት ዘርፎች እንደ አንድ ሴክተር ተነጥሎ የሚታይ ሳይሆን የአጠቃላይ ሀገር አቀፍ ልማት መሰረት ሆኖ የሚያገለግል ቁልፍ ዘርፍ ነው፡፡ **ነእፓ** ትምህርት ለሀገራችንና አጠቃላይ ለሰው ልጆች ስልጣኔ የተጫወተውን ቁልፍ ሚና ከግምት ውስጥ በማስገባትና በልማት ወደፊት የተራመዱ የዓለም ሀገራትን **“ሚስጥረ-እድገት”** በጥልቀት በመመርመር **“ትምህርት-መር ብሄራዊ የልማት ስትራቴጂ”** ለሀገራችን ሁለንተናዊ እድገት እና ብልጽግ ወሳኝ ነው ብሎ ያምናል፡፡

ከዚህ እምነት በመነሳት ትምህርትና ስልጠናን ጨምሮ ሌሎች የሰው ኃይል ልማት ፕሮግራሞች **የነእፓ** ሀገራዊ የልማት ፍልስፍና እና ፖሊሲዎች የመሰረት ድንጋይ ሆነው ለሚቀጥሉት በርካታ አመታት ያገለግላሉ፡፡ ይህ **ትምህርት-መር የልማት ስትራቴጂ** ሀገራችንን በአጭር ግዜ ውስጥ ካለችበት አስከፊ ድህነት አላቆ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች መሀል ለማስገባት በሂደትም በዓለም የበለጸጉ አገሮች ከበብ ውስጥ ቦታ እንድትይዝ ዋነኛው የፖሊሲ ማዕቀፍ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚህም መሰረት የትምህርት ዘርፍ የሀገራችን ሁለንተናዊ ልማት እና ብልጽግና የመሰረት ድንጋይ በማድረግ ሁሉም የመንግስት የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የሰው ኃይል ልማትን ያማከሉ ይሆናሉ፡፡

### 3.2 ጤና

በሀገራችን ከተንሰራፉ ማህበራዊ ቀውሶች አንዱ ጤና ነው፡፡ የሀገራችን የጤና ተቋማት በብዛት፣ በጥራትና በአደረጃጀት ኋላ ቀር ናቸው፡፡ የመንግስትም ሆነ የግል የጤና ተቋማት ብዛት ከሀገራችን የህዝብ ብዛት አንጻር ሲታይ እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ዜጎች በቂ የህክምና አገልግሎት በአካባቢያቸው ማግኘት አይችሉም፡፡ ከዚህ ባሻገር የጤና ተቋማት ስርጭት ፍትሀዊነት የጎደለውና በጥቂት የክልል ዋና ከተሞች ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ የጤና ባለሙያዎች ብዛት፣ የህክምና መሳሪያዎችና የመድሀኒት አቅርቦት ከፍተኛ እጥረት የጤና ዘርፉን ችግሮች ይበልጥ ከባድና የተወሳሰበ አድርጎታል፡፡ **ነእፓ** የሀገራችን የጤና ዘርፍ ያሉበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለማስወገድና ህዝባችን ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት እንዲችል የሚከተሉትን የጤና ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

1. የጤናን ሁለተናዊ እሳቤን መሠረት ባደረገ መልኩ የህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ፖሊሲ ይቀረፃል፣
2. ጤናማና ደህንነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ ለመገንባት የጤናው ሴክተር ከሌሎች ሴክተሮች ጋር እንዲቀናጅ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም ሌሎች ለጤናው ዘርፍ ልማት በቀጥታና በተዘዋዋሪ አስተዋፅዖ ያላቸው ሴክተሮች፤ ትምህርት፣ ውሃ፣ ግብርና፣ ድህነት ቅነሳ፣ ፋይናንስና ኢኮኖሚ፣ ንግድና ኢንዱስትሪ፣ መንገድና ትራንስፖርት፣ ብዙሀን መገናኛ የመሳሰሉትን ከጤናው ሴክተር ጋር በተቀናጀ መልኩ የሚሰሩበት ስርዓት ይዘጋጃል፣
3. በሽታን አስቀድሞ ለመከላከል ልዩ ትኩረት የሚሰጥ፣ ተገቢውን ህክምና በወቅቱ ማቅረብ የሚችል፣ ህሙማን ከህመማቸው አገግመው ወደ ዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው እንዲገቡ የሚያደርግ የጤና አገልግሎት ሥርዓት ተቀርጾ ተግባራዊ ይደረጋል፣
4. ተላላፊ በሽታዎች በአብዛኛው የህብረተሰባችን ክፍል ዋነኛ የጤና ቀውስ ብሎም የሞት መንስኤ ናቸው፡፡ ተላላፊ በሽታንና ወረርሽኝ መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችል የማህበረሰቡን ተሳትፎና ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ዘላቂ ስትራቴጂ ተነድፎ ተግባራዊ ይሆናል፣
5. በሀገራችን ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍተዋል፡፡ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ የልብና የስኳር ህመም፣ ካንሰርና ሌሎች በሽታዎች በጤናው ሴክተር ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደሩ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ በአዲስ አበባ ከሚሞቱት ሰዎች ውስጥ ከ50% በላይ የሚሆኑት ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከልና ለማከም የፖሊሲ ማዕቀፍ ተቀርጾ ስራ ላይ ይውላል፣
6. ጤናማ የሆነ የአኗኗር ዘይቤ የማህበረሰብ ልማድ እንዲሆን መንግስት ድጋፍና ማበረታቻ የሚሰጥበት አግባብ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፣
7. የአዕምሮ ጤናው ያልተጠበቀ ማህበረሰብ ጤናው የተሟላ ሊሆን አይችልም፣ ስኬታማ ህይወትን መምራትም አይችልም፡፡ የአዕምሮ ጤና ችግር በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች በስፋት የሚታይ ቢሆንም በመስኩ የሚሰጠው የጤና አገልግሎት ከፍተኛ የተደራሽነትና ጥራት ውስንነት ይታይበታል፡፡ የአዕምሮ ጤና አገልግሎት ከሌሎች የጤና አገልግሎት በተቀናጀ ሁኔታ ለሁሉም ማህበረሰብ ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፣
8. በሀገራችን የእናቶችና የህፃናት ሞት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ ቢመጣም ዛሬም ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሚባል የጨቅላ ህጻናትና የእናቶች ሞት ከሚከሰትባቸው ሀገራት አንዷ ነች፡፡ የሕፃናት፣ አፍላ ወጣቶችና እናቶችን ጤንነትና ደህንነት በተሟላ መልኩ የሚያስጠብቅ ስትራቴጂ ይዘጋጃል፣
9. የተመጣጠነ የምግብ እጥረት ለተለያዩ ተላላፊ እና ተላላፊ ላልሆኑ በሽታዎች ያጋልጣል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ህጻናት ሞት መንስኤዎች ውስጥ ግማሽ ያህሉ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በሀገራችን ያለውን የስርዓተ-ምግብ ሁኔታ ለማሻሻል የጤናው ሴክተር ከሌሎች ሴክተሮች ጋር በተቀናጀ መልኩ የሚሰራበት ስርዓት ተቀርጾ ተግባራዊ ይደረጋል፣

10. ለጤና ጠንቅ የሆኑ እፆች በሀገራችን በከፍተኛ ሁኔታ እየተስፋፉ መጥተዋል፡፡ የአልኮል መጠጦች፣ ትምባሆና አደንዛዥ እፆች የመሳሰሉ ጎጂ ሱሶችን ለማስቆም ጠንካራ ፖሊሲ በመንደፍ የህብረተሰባችን በተለይም የወጣቱ ጤንነትና ደህንነት እንዲጠበቅ ይደረጋል፣
11. ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት ለመስጠት የጤና ባለሙያ ብቃትና ስነ-ምግባር ቁልፍና የማይተካ ሚና አለው፡፡ በመሆኑም በጥናት ላይ የተመሰረተና የሀገሪቱን የበሽታ ስርጭት ያገናዘበ የጤና ስርዓተ-ትምህርት እንዲቀረፅ ድጋፍ ይደርጋል፡፡ በተጨማሪም የጤና ባለሙያዎች ተከታታይ የሥራ ላይ ስልጠና እንዲያገኙ የሚያስችል የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች ተነድፈው ተፈጻሚ ይሆናሉ፣
12. የጤና ባለሙያዎች የኑሮ ሁኔታ አለመመቻቸት ለህብረተሰቡ በሚሰጡት አገልግሎት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የጤና ባለሙያውን ለመደገፍ የተለያዩ የማበረታቻ ፓኬጆች ተቀርጸው በስራ ላይ ይውላሉ፣
13. ጠንካራ የጤና ባለሙያዎች ማህበር መኖር ሙያው የሚጠይቀውን የላቀ አገልግሎት ለመስጠት ቁልፍ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም በተለያዩ የጤናና ጤና ነክ ጉዳዮች ላይ የጤና ባለሙያዎች በማህበር እንዲደራጁና ሙያቸውን እንዲያዳብሩ አስተዳደራዊ ድጋፎች ይሰጣሉ፣
14. መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፣
15. መሠረታዊ የጤና አገልግሎት ማግኘት የሁሉም ዜጋ መብት ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም ዜጎች ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ለማድረግ አቅምን ያገናዘብ የጤና መድህን ሥርዓት ይዘረጋል፣ መንግስት ለጤናው ዘርፍ የሚያደርገው የበጀት ድጎማ ከፍ እንዲል ይደረጋል፣
16. በጤናው ዘርፍ የሚስተዋለውን የግብዓት ችግር ለመቅረፍ መድሀኒትና ሌሎች የጤና ግብዓቶች በሀገር ውስጥ በጥራት እና በበቂ ሁኔታ እንዲመረቱ ማበረታቻ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የጤና ግብዓቶች አያያዝና ስርጭትን ዘመናዊና ያልተማከለ እንዲሆን የተሻሻሉ ሥርዓቶች ይዘረጋሉ፣
17. የጤና ተቋማትን የመረጃ አያያዝ እና ትስስር ለማሻሻል፣ የጤና አገልግሎት አሰጣጡን ለማቀላጠፍ እና ለማዘመን ኢ-ሄልዝ (e-health) እና ሌሎች የጤና አገልግሎቱን ለማሻሻል የሚረዱ ቴክኖሎጂዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡
18. በጤና መስክ ጥናትና ምርምር ማድረግ የተሻለ የህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ሥራዎችን ለመስራት ጉልህ አስተዋፅዖ አለው፡፡ በጤና ላይ የሚሰሩ ጥናቶች እንዲስፋፋና የህብረተሰቡን የጤና ችግሮች ለመፍታት የሚያግዙ የፖሊሲ ግብዓት መሆን እንዲችሉ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የምርምር ማዕከሎች ጋር በጋራ የሚሰራበት ስርዓት ይዘጋጃል፣
19. ጤናውና ደህንነቱ የተጠበቀ ማህበረሰብ ለመፍጠር መንግስት፣ የሲቪክ ማህበራትና የግሉ ሴክተር በቅንጅት የሚሰሩባቸው መድረኮች ይመቻቻሉ፡፡

## 3.3 ከተማና ቤቶች ልማት

ውብ፣ ዘመናዊ፣ ምቹና ንጹህ ከተሞች እና አካባቢዎች ለዜጎች ሁለንተናዊ ህይወት እጅግ አስፈላጊ ናቸው፡፡ ዜጎች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎቻቸውን በተሳካ ሁኔታ ለመከወን እንዲችሉ ብሎም የአካልና የአዕምሮ ጤናው የተጠበቀ ማህበረሰብ ለመፍጠር ዘመናዊ እና ለኑሮ ምቹ የሆኑ ከተሞች እንዲሁም በቂ እና ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው የመኖሪያ ቤቶች መገንባት ያስፈልጋል፡፡ የከተሞች እና ቤቶች ዲዛይንና ግንባታ የአንድን ማህበረሰብ ስልጣኔ ማሳያ እና የባህል መገለጫዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም ለመኖሪያ፣ ለስራ፣ ለትምህርትና ለመዝናናት ምቹ ብሎም ለአካባቢ ጥበቃ ልዩ ትኩረት በሚሰጥ መልኩ ከተሞችን መገንባትና ማስተዳደር **ነእፓ** ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ፕሮግራሞች ውስጥ ነው፡፡

### 3.3.1 የከተማ ልማት

የሀገራችን የከትመት ምጣኔ 20% ያልዘለለ ሲሆን ይህም ከሰሀራ በታች ካሉ በርካታ የአፍሪካ ሀገሮች ጋር እንኳ ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው፡፡ በአንጻሩ አዲስ አበባን ጨምሮ አንዳንድ የክልል ከተሞች በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ይገኛሉ፡፡ በ2010 በሀገራችን 971 ከተሞች የነበሩ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከ100,000 (መቶ ሺህ) በላይ ህዝብ ያላቸው 17 ከተሞች እንዲሁም ከ2000 (ሁለት ሺህ) ህዝብ በላይ ነዋሪ ያላቸው 803 ከተሞች እንደሆኑ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው በሀገራችን የከተሞች ዕድገት አለመመጣጠን አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን ነው፡፡ ያልተመጣጠነ የከተሞች ዕድገት የከተሞች የመሠረተ-ልማት አቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ የተዛባ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ከህዝብ ቁጥር ዕድገት ጋር የሚጣጣም፣ በጥናትና መረጃ ላይ የተመሰረተ፣ ለነዋሪዎች በቂ እና ጥራት ያለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶችን መስጠት የሚያስችል የከተማ ልማት ፕሮግራም መንደፍ ያስፈልጋል፡፡ የከተሞችን ዕድገት ከሚያዛቡ እና ጤናማ ዕድገት እንዳይኖር ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱና ዋነኛው ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰትን ለመቀነስ የሚያስችል የተቀናጀ የከተማ ልማትና የገጠር ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

### 3.3.2 የቤቶች ልማት

የመኖሪያ ቤት እጥረት በሀገራችን ከሚስተዋሉ ቁልፍ ማህበራዊ ችግሮች አንዱ ሲሆን በሀገራችን ካለው ፈጣን የህዝብ ቁጥር አንጻር ችግሩ በየጊዜው እየጨመረ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ በከተሞች አካባቢ ያለው የቤት ፍላጎት እና አቅርቦት ሰፊ ልዩነት ያለው ሲሆን ይህም በከተሞች ውስጥ ያለውን የመኖሪያ ቤት ችግር እጅግ አባብሶታል፡፡ ሀገራችን ውስጥ በሁሉም አካባቢዎች ባለው ከፍተኛ የቤት ችግር ሳቢያ በተጨናነቀ ሁኔታ የሚኖሩ ቤተሰቦች ቁጥር፣ ደባልነት እና ቤት-የለሽነት /Homelessness/ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡

ለመኖሪያ ቤት ችግር መስፋፋት የሚከተሉት ምክንያቶች በግምባር ቀደምነት ይጠቀሳሉ፣

- የተሳሳተ የመሬት ኪራይ አስተዳደር እና አሰራሩ የፈጠረው የመሬት አቅርቦት ዝቅተኛ መሆን፣
- ለቤት ግንባታ የሚሆን በቂ የፋይናንስ ምንጭ አለመኖር፣
- ኃላፊነት በጎደላቸው የመሬት ነጋዴዎችና የመንግስት ባለስልጣናት በቅንጅት የሚደረግ ህገ-ወጥ የመሬት ቅርምት፣
- ከመሬት ንግድ ወደ ፊት ትርፍ ለማግኘት ሰፊ የከተማ መሬት ጥቅም ላይ ሳይውል እንዲቆይ የሚፈቅድ ብልሹ አሰራር (Speculation)፣
- ከመሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ የተንሰራፋው ከፍተኛ ሙስናና ህግ አልበኝነት፣
- አቅምን ያላገናዘበ የቤት ስታንዳርድ እና ግልፅ የቤት ልማት ፖሊሲ አለመኖር፡፡

እነዚህንና ሌሎች ዘርፈ ብዙ የመኖሪያ ቤትና ተያያዥ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚከተሉት ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

1. የዜጎች የመኖሪያ ቤት ማግኘት ጉዳይ መሰረታዊ የሰብዓዊ መብት ጥያቄ ተደርጎ እንዲወሰድ የሚያደርጉ ህጎችና ፖሊሲዎች እንዲወጡ ይደረጋል፣
2. መንግስት ለመኖሪያ ቤት ግንባታ ከፍተኛ ሀብት ይመድባል፣
3. የግል ባለሀብቶች በመኖሪያ ቤት ግንባታ እንዲሳተፉ ማበረታቻ ይሰጣል፣
4. መኖሪያ ቤት መገንባት/መግዛት የሚሹ ወገኖች ከገንዘብ ተቋማት የረዥም ጊዜ ብድር በአነስተኛ ዋጋ የሚያገኙበት መንገድ ይመቻቻል፣
5. የመኖሪያ አካባቢዎች በቂ እና ምቹ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

6. በአነስተኛ ወጪ እና በቀላል ቴክኖሎጂ የሚገነቡ ቤቶች እንዲስፋፉ ፕሮጀክቶች ተነድፈው ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
7. ውጤታማ የቤት ልማት ፕሮግራሞችን ዕውን ለማድረግ የሚረዱ ጥናቶችን ለማካሄድና ዓለም-ዓቀፍ ተሞክሮዎችን ለመቅሰም የሚረዱ መድረኮችን ከባለድርሻ አካላት ጋር ለማዘጋጀት የሚያግዝ አሰራር ይዘረጋል፡፡

### 3.4 ወጣቶች

ከሀገራችን ህዝብ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ወጣቶች ለሀገራችን ሁለንተናዊ ዕድገት መሰረት እና ዋስትና ናቸው፡፡ የነገዋ ኢትዮጵያ ዕጣ ፋንታ እና ተስፋ በዛሬዎቹ የሀገራችን ወጣቶች ይወሰናል፡፡ የሀገራችን አንድነት፣ ሰላምና ብልጽግና የሚወሰነው ዛሬ ለወጣቶቻችን በምንሰጠው ትኩረት፣ ወጣቶቻችንን ለማልማት በምንሰራው ስራና ለዚሁ በምናፈሰው ሀብት ነው፡፡ ወጣቶች እምቅ የማሰብ እና የመስራት ኃይል፣ ፍላጎት፣ ድፍረት፣ ስጋትን የመቀበል (Risk taking) ዝንባሌ ያላቸው ሲሆን እነዚህ የወጣትነት ባህሪያት በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ከተደረገ ሀገርን ለማሳደግ መልካም አጋጣሚዎች ይሆናሉ፡፡

በሀገራችን ታሪክ ወጣቶች በፖለቲካው ዘርፍ አምባገነን ስርዓቶችን በመታገል ለሀገር ትልቅ ውለታ ውለዋል፣ በኢኮኖሚው መስክ በገጠር እና በከተማ፣ በግብርና፣ በኢንደስትሪና በአገልግሎት ሰጭ መስኮች ተሰማርተው ወደር የማይገኝለት ስራ በመስራት ላይ ናቸው፡፡ በአንጻሩ ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነ የሀገራችን ወጣቶች ለከፋ ስራ አጥነትና ተያያዥ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተጋልጠው ለአስከፊ የህይወት ውጣ ውረድ ተዳርገዋል፡፡ **ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** የሀገራችንን ወጣቶች ዘርፈ ብዙና ጥልፍልፍ ችግሮች ለመቅረፍ ብሎም ወጣቶች ለሀገራችን ልማትና ብልጽግና ሁነኛ ሚና ይኖራቸው ዘንድ የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል፡፡

1. ለወጣቶች የስራ ዕድል ለመፍጠር የሚያስችሉ ልዩ ልዩ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ተቀርጸው ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
2. ወጣቶች በሀገራችን ዘላቂ ልማት፣አስተማማኝ ሰላም እና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ውስጥ ጠንካራ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፣
3. ወጣቶችን በአካልና በስነ-ልቦና እንዲታነጹ እና ከጎጂ ልማዶች እንዲጠበቁ በቂ የስፖርት ማዘውተሪያና መዝናኛ ስፍራዎች እንዲኖራቸው ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፣
4. ወጣቶች ተደራጅተው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መብቶቻቸውን ማስከበር ይችሉ ዘንድ በቂ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ድጋፍ እንዲያገኙ የሚያግዝ አሰራር ይዘረጋል፣
5. ወጣቶች በቂ ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኙ፣ የምርምርና የፈጠራ አቅማቸው እንዲዳብር መንግስት በቂ ሀብት ይመድባል፣ ወጣቶች ከፍተኛ የማንበብ ባህል እንዲያዳብሩ የፌደራልና የክልል መስተዳድር አካላት ምቹ ሁኔታን እንዲፈጥሩ ይደረጋል፣
6. ወጣቶች የዛሬዋ እና የነገዋ ኢትዮጵያ መምህራን፣ ሳይንቲስቶች፣ ሀኪሞች፣ ፖሊሶች፣ ወታደሮች፣ ስራ ፈጣሪዎችና ኢንቨስተሮች፣ ተመራማሪዎች፣ ፖለቲከኞችና የህዝብ አስተዳዳሪዎች፣ የጥበብ ሙያተኞች፣ . . . ናቸው፡፡ በመሆኑም የወጣቶች ልማት እና የሀገር ልማት የማይነጣጠሉና የተቆራኙ አድርጎ በመውሰድ ከፍተኛ የፖሊሲ ትኩረት ይሰጣል፣ በቂ መዋዕለ-ንዋይ ይመደባል፣
7. የወጣቶችን ለበሽታ ተጋላጭነት ለመቀነስ የሚረዱ የወጣቶች ጤና እንክብካቤ እና ድጋፍ የሚደረግበት ስርዓት ይዘረጋል፣ ወጣቶች የስነ-ጾታ ግንዛቤያቸው ከፍ እንዲል በቂ የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፣
8. በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች የሚኖሩ ወጣቶች እርስ በእርስ እንዲተዋወቁ፣ መልካም ተሞክሮዎቻቸውን እንዲለዋወጡና የባህል መስተጋብር እንዲፈጥሩ ልዩ ልዩ መድረኮች ይዘጋጃሉ፣

9. ወጣቶች የሀገርና የህዝብ ፍቅር እንዲኖራቸው፣ ሀገራዊ እሴቶቻችንን ጠብቀው እና ከጎጂ መጤ የባህል ተፅዕኖ ተጠብቀው መኖር እንዲችሉ አስፈላጊ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

### 3.5 ሴቶችና ህጻናት

በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ሀገሮች ሴቶች እና ህጻናት በተለያዩ የተሳሳቱ ልማዶችና ጎጂ አስተሳሰቦች ምክንያት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መብቶቻቸው ሲሸራረፉና ጥቅሞቻቸው ሲጓደሉ ማየት የተለመደ ክስተት ነው፡፡ የሴቶችና ህጻናት መብቶች ከአጠቃላይ የሰብዓዊ መብቶች የማይነጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው፡፡ የሴቶችና ህጻናት መብቶች የማይከበርበት ሀገር እና ማህበረሰብ ለሰብዓዊ መብት መከበር የሚኖረው ግንዛቤና አተገባበር የተሟላ ሊሆን አይችልም፡፡ በሳይንስና ቴክኖሎጂ የበለጸጉ እና የተሻለ የሰብዓዊ መብት አያያዝ እንዳላቸው የሚነገርላቸው ሀገሮች ሳይቀር የሴቶችን መብት በማክበር እና የህጻናትን መብት ከመጠበቅ አንጻር ያላቸው ታሪክ የደበዘዘ ነው፡፡ በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ድሀ ሀገሮች ሴቶች ለጾታዊ ጥቃትና ትንኮሳ፣ ታዳጊ ህጻናት ለከፋ የጉልበት ብዝበዛ የተዳረጉ ናቸው፡፡

በእውቀትና በመልካም ስነ ምግባር የታነጸ ትውልድ ለመገንባት ትልቁን ሚና የሚጫወቱት ሴቶች እንደ እናት፣ እህት እና እንደ ልጅ ልዩ ትኩረትና እንክብካቤ ሊደረግላቸው፣ መብቶቻቸውን ከሚሸራርፉ ልማዶች፣ ጎጂ ባህሎችና አሰራሮች እንዲጠበቁ ተገቢ የህግ ከለላ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የነገ ሀገር ተረካቢ ህጻናት በአካል፣ በእውቀት፣ በስነ-ምግባር እና በስነ-ልቦና ተገንብተው የነገዋን ኢትዮጵያ በተሻለ ደረጃ ማበልጸግና ማስተዳደር ይችሉ ዘንድ ልዩ የፖሊሲ ትኩረት ይሻሉ፡፡

**ነጻነትና እኩልነት ፓርቲ** ከሀገራችን ህዝብ ከግማሽ በላይ የሆኑትን የሀገራችን ሴቶችና ህጻናት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞቻቸው እንዲከበሩ፣ ከአስተዳደራዊ መድሎ እንዲጠበቁ፣ ከጾታዊ ጥቃትና ኢ-ፍትሀዊ የጉልበት ብዝበዛ ከለላ እንዲያገኙ ልዩ ትኩረት አድርጎ ይሰራል፡፡ **ነእፓ** ለዘመናት ስር ሰደው የቆዩ ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ልማዶች፣ ወጎችና አስተሳሰቦች በሴቶችና ህጻናት ላይ ያደረሱትን ዘርፈ ብዙ ጫናዎችና ተግዳሮቶች ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ የተቀናጀ የፖሊሲ እና የአሰራር ስርዓቶች እንዲዘረጉና ተግባራዊ እንዲሆኑ ሳያሰልስ ይሰራል፡፡ የሴቶችና ህጻናት መብትና ጥቅሞችን ለማስከበር ከምንም በላይ የአመለካከት እና የአስተሳሰብ ለውጥ መኖር እንዳለበት የሚያምነው **ነእፓ** ከሴቶችና ህጻናት አንጻር የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ይከተላል፡፡

#### ሴቶችና ህጻናትን በተመለከተ

1. ሴቶችና ህጻናትን በተመለከተ በሀገር-ዓቀፍ፣ አህጉር-ዓቀፍ እና በዓለም-ዓቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያገኙ ህጎችና ስምምነቶች የሴቶችንና ህጻናትን መብቶች በሚያስጠብቅ መንገድ ተግባራዊ እንዲሆኑ ይሰራል፣

2. በማዕከላዊ መንግስት እና በክልል መስተዳድር አካላት የሚወጡ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የሴቶችና ህጻናትን መብቶችና ጥቅሞች በልዩ ሁኔታ የሚያከብሩና የሚያስከብሩ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

3. ሴቶችና ህጻናትን በተመለከተ የተሳሳቱና ጎጂ ልማዶች፣ አስተሳሰቦች፣ አሰራሮች ወዘተ ለመቀየርና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራሉ፤

4. የሴቶችንና ህጻናትን ማህበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ፍትሀዊ ተጠቃሚት ለማረጋገጥ የሚያግዙ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣

5. በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚደርሱ ህገወጥ እና ኢ-ሞራላዊ ጥቃቶችና ትንኮሳዎች ሙሉ ለሙሉ ይቆሙ ዘንድ ህጋዊ እና አስተዳደራዊ ማዕቀፎች እንዲዘረጉ ይደረጋል፡፡

**ሴቶችን በተመለከተ**

1. የሴቶችን የትምህርት ተሳትፎ የሚያሳድጉና የሴቶችን መጠነ ማቋረጥ (Drop out) የሚቀንሱ አሰራሮች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣ ልዩ የማበረታቻ ድጋፎች የሚያገኙበት አሰራር ይዘረጋል፣

2. ሴቶች በመንግስት፣ በግል፣ መንግስታዊ ባልሆኑ እና ዓለም-ዓቀፍ ድርጅቶች ተመጣጣኝ የስራ ዕድል እንዲያገኙ የሚያግዝ የህግ ማእቀፍና አሰራር ይዘረጋል፣ ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብታቸው እንዲከበር አስፈላጊ የህግ ማዕቀፎች እንዲዘጋጁ ይደረጋል፣

3. ሴቶች በቂ የወሊድ እረፍት ከሙሉ ክፍያ ጋር፣ እንዲሁም ተጨማሪ እረፍት ያለክፍያ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

4. በተለያየ የትምህርት ደረጃ ላይ ያሉ ሴቶች ከጾታዊ ትንኮሳ ተጠብቀው ትምህርታቸውን በነጻነት እና በትጋት መከታተል እንዲችሉ የሚያግዙ የሴቶች ትምህርት ቤቶች (**የአንድ ጾታ ትምህርት ቤቶች**) በመንግስት፣ በግሉ ሴክተርና በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እንዲስፋፉ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፣

5. በአብዛኛው የሀገራችን ህዝቦች ተቀባይነት የሌላቸው ጾታዊ መስተጋብሮች፣ የሴቶችን ሰብዓዊ ክብር የሚያረክሱ መጤ ወግና ባህሎች፣ ድርጊቶችና አሰራሮች እንዲወገዱ ይደረጋል፣

6. ከቅድመ ትምህርት እስከ ከፍተኛ ትምህርት በሚዘጋጁ ስርዓተ-ትምህርቶች ውስጥ ስርዓተ-ጾታ በቂ ትኩረት እንዲያገኝና ጾታዊ መድሎን ሊፈጥሩ የሚችሉ የትምህርት ይዘቶች እንዲሻሻሉ ወይም ሙሉ ለሙሉ እንዲወገዱ ይደረጋል፣

7. ሴቶች ተደራጅተው መብታቸውን እና ጥቅሞቻቸውን ያስከብሩ ዘንድ ልዩ ልዩ የሴቶች ማህበራት እና ድርጅቶች፣ የጥናትና ምርምር ተቋማት ወዘተ ማቋቋም እንዲችሉ ልዩ ድጋፍ ይደረጋል፣

8. የሴቶች፣ የእናቶች እና የእህቶች ቀን በሀገር ዓቀፍ ደረጃ በደመቀ ሁኔታ እንዲከበሩ በማድረግ ባለድርሻ አካላት እና ዜጎች ሴቶችን በተመለከተ ያላቸው አመለካከት እንዲስተካከል የሚያግዙ አሰራሮች ይዘረጋሉ፣

9. በተለይም የገጠሯን ሴት የኑሮ ጫና ሊቀንሱ፣ ማህበራዊ ሸክሟን ሊያቃልሉ እና ሰብዓዊ መብቶቿ ሳይሸራረፉ እንዲከበሩ ሊያደርጉ የሚችሉ አሰራሮች ልዩ ትኩረት ይሰጣቸዋል፣

10. ሰላምን፣ መቻቻልን እህትማማችነትን/ወንድማማችነትን በማስፈን ረገድ ሴቶች ያላቸውን ተፈጥሯዊ ክህሎትና ዝንባሌ እንዲጠቀሙ፣ ሴቶች በግጭት አፈታትና እርቅን በማውረድ ስራዎች ውስጥ እንዲሳተፉ በማድረግ በሰላም ግንባታ ቁልፍ ሚና እንዲጫወቱ ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡

**ህጻናትን በተመለከተ**

1. ህጻናት የስነ-ልቦናና አካላዊ ደህንነታቸው ተጠብቆላቸው ደስተኛ ሆነው እንዲያድጉ የሚያስችል የተቀናጀ የህጻናት ድጋፍና እንክብካቤ ፕሮግራሞች ይቀረጻሉ፣

2. የህጻናት የነገ ህይወት የሚወሰነው ከምንም በላይ ዛሬ ላይ በሚያገኙት ትምህርትና እውቀት በመሆኑ፣ በየትኛውም የሀገራችን ክፍል፣ በከተማም ይሁን በገጠር የሚኖሩ ህጻናት የትምህርት አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣

3. የህፃናት ጤና በተሟላ ሁኔታ እንዲጠበቅ፣ ከተለያዩ በሽታዎች የሚከላከሉ በቂ ክትባቶች በወቅቱና በአግባቡ እንዲያገኙ በሀገሪቱ የጤና ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ተገቢ ትኩረት እንዲሰጠው ይደረጋል፣

4. በሰው ሰራሽም ይሁን በተፈጥሮ አደጋዎች ጉዳት የሚያጋጥማቸው ህጻናት ልዩ እንክብካቤ እንዲያገኙ፣ የአደጋ ተጋላጭነታቸው እንዲቀንስ ይደረጋል፣

5. ለህጻናት የተሟላ አካላዊ እና ስነ-ልቦናዊ ዕድገት እገዛ የሚያደርጉ በቂ የመጫወቻ እና መዝናኛ ቦታዎች ይኖሩ ዘንድ በከተሞች ፕላን ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፣

6. ህጻናት ለህገወጥ የጉልበት ብዝበዛ (Child labor) እንዳይዳረጉ የሚከላከል በቂ የህግ ከለላ እንዲኖር ይደረጋል፣ በዚህ ተግባር ላይ የሚሰማሩ አካላትን ለመቆጣጠርና ጠንካራ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፣

7. የነገ ሀገር ተረካቢ ህጻናት ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው፣ ልምድ የሚቀስሙበትና ልምምድ የሚያደርጉበት መድረክ ይኖራቸው ዘንድ ጠንካራ ሀገር አቀፍ የህጻናት ጥምረትና የህጻናት ፓርላማ እንዲኖር ይደረጋል፣

8. ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ህጻናት በቂ እንክብካቤና ድጋፍ የሚያገኙበት አሰራር ይዘረጋል፣ የአዕምሮ ዝግመት ላለባቸው ህጻናት ተገቢ የትምህርት ፕሮግራሞች ይዘጋጃሉ፣

9. ህጻናት የልደት ምስክር ወረቀትና ሌሎች የወሳኝ ሁነት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ወላጆችና ማህበረሰቡ በቂ ትምህርትና ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያስችል ስራ ይሰራል፣

10. ጨቅላ ህጻናት በሚኖሩበት አካባቢ የቅድመ ትምህርት አገልግሎት የሚያገኙበት አሰራር ይዘረጋል፡፡

### 3.6 ኃይማኖት

ለዜጎች የተሟላ ስብዕናና ሁለንተናዊ ደህንነት ኃይማኖት ያለው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ በአካልና በስነ-ልቦና የጠነከረ ትውልድ ለመፍጠር ኃይማኖቶች የማይተካ ሚና አላቸው፡፡ በማህበረሰብ ዕድገትና ደህንነት ላይ የተሰሩ ልዩ ልዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በትክክለኛ እውቀት ላይ የተመሰረተ፣ ሚዛናዊ የሆነ የቁስ እና መንፈሳዊ ዕድገት ለጤናማ ማህበረሰብ ግንባታ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን ለኃይማኖትና ኃይማኖተኛነት የሚሰጡትን ከፍተኛ ዋጋ እንዲሁም ኃይማኖት በህብረተሰብ ዕድገት ላይ ያለውን በሳይንስ የተረጋገጡ ሀቆች ታሳቢ በማድረግ **ነእፓ** ኃይማኖትን በተመለከተ የሚከተሉትን የፖሊሲ አቅጣጫዎች ይከተላል፡፡

1. ሁሉም ኃይማኖቶች እኩል ናቸው፣ ኃይማኖትን ከኃይማኖት ወይም የአንድን ኃይማኖት ተከታዮች ከሌላው ኃይማኖት ተከታዮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሊያበላልጡ የሚችሉ አሰራሮች፣ ወጎችና ልማዶች አይኖሩም፣
2. መንግስትና ኃይማኖት የተለያዩ ይሆናሉ፡፡ መንግስት በኃይማኖት ተቋማት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፣ እንዲሁም የኃይማኖት ተቋማት በመንግስት ተቋማት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አይገቡም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስትና የሀይማኖት ተቋማት የጋራ በሆኑ አጀንዳዎች ዙሪያ በትብብርና በቅንጅት ሊሰሩ ይችላሉ፣

3. ማንኛውም ሰው የፈለገውን እምነት የመከተልና የማስፋፋት ነጻነት አለው፣ በኃይማኖት ማስገደድ አይኖርም፣
4. የአንድ ኃይማኖት ተከታዮች ባሉበት አካባቢ የእምነት ተቋሞቻቸውን የመገንባት ነጻነት አላቸው፣ መንግስት እንደ አስፈላጊነቱ የእምነት ተቋማት የሚገነቡበት ቦታ ሊሰጥ ይችላል፣
5. የአንድ ዕምነት ተከታዮች በሚበዙበት ክልሎችና አካባቢዎች ለሚኖሩ፣ በቁጥር አናሳ የሌላ እምነት ተከታዮች እምነታቸውን በነጻነት የማራመድ፣ የእምነት ተቋሞቻቸውን የመገንባት፣ የእምነት ተከታዮቻቸውን የማስተማር ወዘተ መብታቸው ይከበራል፣
6. በእምነቶች መካከል እውነተኛ መቻቻል እንዲኖር፣ የተለያየ እምነት ተከታዮች ተከባብረውና ተቻችለው እንዲኖሩ በእምነቶች መካከል ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር ምቹ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፣
7. የማናቸውንም እምነት ተከታዮች በእምነታቸው እንዲሸማቀቁና እንዲሰጉ የሚያደርጉ ቢሮክራሲያዊ፣ ህጋዊ፣ የሚዲያና የፖለቲካ ስራዎች አይኖሩም፣
8. የሁሉም ኃይማኖቶች መሰረታዊ መልዕክት ሰላም፣ ፍቅር፣ ሰብዓዊነትና ወንድማማችነት ነው ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚህ መሰረት ማንኛውንም ኃይማኖት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሽብርና ፀጥታ መደፍረስ ጋር የሚያገናኝ አመለካከትና አሰራር አይኖርም፣
9. የኃይማኖት ምሁራንና የኃይማኖት ተቋማት ለሀገር ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም ለዘላቂ ልማት መረጋጋጥ የድርሻቸውን እንዲወጡ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡

### 3.7 ስፖርት

1. በአካልና በመንፈስ የዳበረ ዜጋን ለመፍጠር ስፖርት ትልቅ ሚና እንዲጫወት ተገቢ የፖሊሲ ትኩረትና ድጋፍ ይደረጋል፣
2. ዜጎች ለስፖርት ፍቅርና ዝንባሌ እንዲያድርባቸው የሚያደርጉ ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ተግባራዊ ይደረጋሉ፣
3. ትምህርት ቤቶች የስፖርተኞች መፍለቂያ እንዲሆኑ ለማስቻል በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ በበቂ ሁኔታ ትኩረት እንዲሰጠው ይደረጋል፣ ትምህርት ቤቶች አስፈላጊ የስፖርት ቁሳቁሶችና ለስፖርታዊ እንቅስቃሴ ምቹ አካባቢ እንዲኖራቸው በቂ ድጋፍ ይደረጋል፣
4. ባህላዊ ስፖርቶች እዲዳብሩና እንዲጠናከሩ ክልላዊና ብሄራዊ ውድድሮች በስፋት እንዲዘጋጁ ይደረጋል፣ የሀገራችን ባህላዊ ስፖርቶች በአፍሪካና በዓለም ደረጃ እውቅና እንዲያገኙ ለማድረግ የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ይደረጋል፣
5. ስፖርት ከማህበረሰብ ጤና ጋር እንዲያያዝ ከጤናው ሴክተር ጋር በቅንጅት የሚሰራበት አሰራር ይመቻቻል፣
6. የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች እንዲስፋፉና በከተሞች ፕላን ውስጥ ተገቢ ትኩረት እንዲያገኙ ይደረጋል፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎችን በማቋቋም የግሉ ዘርፍ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሳተፉ ድጋፍና ማበረታቻ ይደረጋል፣
7. ስፖርታዊ ውድድሮች ለሰላም፣ ለአብሮነት፣ ለማህበራዊ መስተጋብር፣ በህዝቦች መካከል የፍቅርና የአንድነት ድልድይ ለመገንባት አስተዋፅዖ ማድረግ እንዲችሉ ባለድርሻ አካላት በጋራ የሚሰሩበት የአሰራር ማዕቀፍ ይዘጋጃል፣
8. ስፖርት በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች በእኩል እንዲስፋፋ ይደረጋል፣ በስፖርታዊ እንቅስቃሴ ዝቅተኛ አፈጻጸም ላላቸው አካባቢዎች ድጋፍ ይደረጋል፣
9. ሀገራችን በዓለም ደረጃ እውቅና ባገኘችባቸው የስፖርት ዓይነቶች የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ እንድትችል ልዩ ድጋፍ ይደረጋል፣
10. የስፖርት ፌዴሬሽኖች ራሳቸውን ችለው እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችል አደረጃጀትና ነጻነት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

### 3.8 የአካባቢ ጥበቃ

የአካባቢ ጥበቃ ለዘላቂ ልማት ያለው ጠቀሜታ ዓለም-ዓቀፍ እውቅና እና ድጋፍ እያገኘ መጥቶ በአሁኑ ሰዓት ወሳኝ የፖሊሲ አጀንዳ ሆኗል፡፡ የበረሃማነት መስፋፋት፣ የአካባቢ ብክለት፣ የአፈር መሸርሸር፣ የደን መመናመን፣ የወንዞችና ሀይቆች የውሀ መጠን መቀነስ ወዘተ በተለይም የግብርናውን ዘርፍ ምርትና ምርታማነት በመቀነስ ለሰዎች ደህንነት ከፍተኛ ስጋት ሆኗል፡፡ ለአካባቢ መጎሳቆል  በተለይ በኢንዱስትሪ የበለጸጉ ሀገሮች ወደ ከባቢ አየር የሚለቁት የተበከለ ጭስና ኬሚካል ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ በታዳጊ ሀገሮችም የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ ያለው አነስተኛ ግንዛቤና ደካማ የፖሊሲ ማዕቀፍ ለችግሩ መስፋት ጉልህ አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡

በሀገራችን የአካባቢ ብክለትና የደኖች መመናመን ከጊዜ ወደ ጊዜ ብሄራዊ ስጋት እየሆነ የመጣ ሲሆን የመንግስት ትኩረት ማነስና ዝቅተኛ የህብረተሰብ ግንዛቤ በሀገራችን ካለው አስከፊ ድህነት ጋር ተዳምሮ ችግሩን አባብሶታል፡፡ **ነእፓ** የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ለሀገር ኢኮኖሚና ሁለንተናዊ ደህንነት ያለውን ከፍተኛ አስፈላጊነት በመረዳት ለአካባቢ ጥበቃና ተያያዥ ለሆኑ አጀንዳዎች ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ለተፈጥሮ ሀብትና ለአየር ንብረት መጠበቅ በቂ የፖሊሲ ድጋፍ የሚሰጥ **አረንጓዴ ኢኮኖሚ** በሀገራችን ለመገንባት **ነእፓ** የሚከተሉትን የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

1. በህዝብ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ እንዲቀረጽ ይደረጋል፡፡ ፖሊሲውን ሊያስፈጽም የሚችል ጠንካራ ተቋም በፌደራል መንግስትና በክልል መስተዳድር አካላት ይቋቋማል፣
2. ዜጎች ከብክለት ነጻና ጤናማ በሆነ አካባቢ መኖር እንዲችሉ ይደረጋል፣ ህብረተሰቡ በአካባቢ እንክብካቤ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው የሚያግዙ ስራዎች ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባባር ይሰራሉ፣
3. የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት የአካባቢ ብክለትን እንዳያስከትል ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፣ ከባቢ አየርን የሚበክሉ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ላይ ቁጥጥር ይደረጋል፣
4. ሰፋፊ እና በህዝብና በመንግስት የሚጠበቁ አረንጓዴ አካባቢዎች እንዲስፋፉ ድጋፍ ይደረጋል፣
5. አማራጭ የሀይል ምንጮችን በመፍጠር የደን መጨፍጨፍን መቀነስ የሚያስችል የተቀናጀ የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፣
6. ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችንና ተረፈ ምርቶችን በድጋሚ ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችል ቴክኖሎጂና አሰራር እንዲስፋፋ ድጋፍ ይደረጋል፣
7. በልዩ ልዩ አካላት የሚገነቡ የልማት ተቋማት ከመገንባታቸው በፊት ከአካባቢያዊና ማህበራዊ አሉታዊ ተጽዕኖ ነጻ መሆናቸው የሚረጋገጥበት የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

# 4 የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ

## 4.1 የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መርሆች

የሀገራችን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ስታራቴጂ ዋነኛ ግብ በሀገር ውስጥ የሚደረገውን ኢኮኖሚያዊ፤ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እቅዶችን ለማሳካት የሚደረውገን ጥረት ማገዝ ነው፡፡ **ነእፓ** አገራችን ያለችበትን ጂኦ-ፖለቲካዊና ጂኦ-ስትራቴጂያዊ እውነታዎች ታሳቢ በማድረግና በአፍሪካ ቀንድ፣ በሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች፣ በመካከለኛው ምስራቅ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ ተለዋዋጭ የዲፕሎማሲና የውጭ ግንኙነት ሁነቶችን ከግንዛቤ በማስገባት ሀገራዊ ጥቅማችንን በተሻለ ሁኔታ ለማስከበር የሚያስችል የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

ሀገራችን ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላትን የረዥም ጊዜ ግንኙነት ታሳቢ ያደረገ፣ የሀገራችንንና የጎረቤት ሀገሮችን የጋራ ጥቅም በሚያስከብር የውጭ ግንኙነት መርህ ላይ የተመሰረተ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ግንኙነት ለመፍጠር ጥረት ይደረጋል፡፡ በአካባቢው የተንሰራፋውን ድህነትና ኋላቀርነት ለመታደግ እንደ ሀገር ከምናደርገው ከፍተኛ ርብርብ ጎን ለጎን ከጎረቤት ሀገሮች ጋር አብሮ መስራት ያለውን ከፍተኛ ፋይዳ የሚረዳው ፓርቲያችን ድንበር ተሻጋሪ በሆኑ ችግሮች፣ ስጋቶችና ተግዳሮቶች ዙሪያ በጋራ ለመስራት የሚያስችል የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡ የ**ነእፓ** የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የሚከተሉትን ዋና ዋና ፕሮግራሞች ይይዛል፡፡

1. የሀገራችን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ መነሻና መድረሻ የዜጎቻችንና የሀገርን ፍላጎትና ጥቅም ማስከበር ሲሆን ማንኛውም የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ተግባሮቻችን ይህንን እውነታ ታሳቢ ያደረጉ ይሆናሉ፣
2. የተሳካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በቅድሚያ የሀገራችንን ሰላም መጠበቅ እንደሚኖርበት እናምናለን፡፡ የሀገራችን ሰላም ከውስጣዊ ጉዳዮች ባልተናነሰ መልኩ በቀጠናው ባለው የሰላም ሁኔታ ይወሰናል፡፡ በመሆኑም የሀገራችንን ሰላም በአስተማማኝ ሁኔታ ለማስከበር በአካባቢያችን ሰላም እንዲሰፍን ከፍተኛ ትኩረት እንሰጣለን፣
3. ሌሎች ሀገሮች በውስጥ ጉዳያችን ጣልቃ እንዲገቡ እንደማንፈቅድ ሁሉ ሀገራችንም በሌሎች ሀገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ አትገባም፣
4. የሀገራችን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ቀረጻ ላይ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተለይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት፣ የሚድያ ተቋማት፣ የንግዱ ማኅበረሰብ ተወካዮች፣ የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ተቋማት፣ የማህበረሰብ ተወካዮች፣ የዲያስፖራ አባላት እንዲሳተፉ ይደረጋል፣
5. ተጨባጭና የተሳካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለመንደፍና ተግባራዊ ለማድረግ አካባቢያዊ፣ አህጉራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ለውጦችን ታሳቢ ያደረገ ጥናትና ትንታኔ በየጊዜው ይደረጋል፣ ለዚህ ስራ በቂ የሰው ኃይል እና ሀብት ይመደባል፣
6. አገራችን የአፍሪካ ህብረትና ሌሎች ዓለም ዓቀፋዊና አህጉራዊ ተቋማት መቀመጫ በመሆኗ ከተቋማቱ ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር የሀገራችንን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በተሻለ መልኩ ተፈፃሚ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፣
7. የሀገራችንን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ስኬታማ ለማድረግ የሀገራችን ዲፕሎማቶች አቅምና ተነሳሽነት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ በመሆኑም የዲፕሎማቶች፣ የልኡካንና የዲፕሎማቲክ ሰራተኞች ምልመላና ምደባ አቅምንና ተነሳሽነት ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል፣
8. በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ጉዳይ እንዲሳተፉ ለማስቻልና ለአገራቸው ሊያበረክቱት የሚችሉትን ጉልህ አስተዋፅዖ ለማሳለጥ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና አሰራሮች ይዘረጋሉ፡፡

## 4.2 ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖረን ግንኙነት

ከጎረቤት ሀገሮቻችን ጋር የረዥም ጊዜና የጠበቀ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት አለን፡፡ ከአንዳንዶቹ የጎረቤት ሀገራት ጋር በተለያዩ ጊዜና ምክንያቶች ቅራኔዎችና ግጭቶች የተከሰቱ ቢሆንም፣ ከጎረቤት ሀገራት ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር እና ይበልጥ ማበልጸግ ይቻላል ብለን እናምናለን፡፡ የሀገራችንን የአጭርና የረዥም ጊዜ ጥቅሞችና ፍላጎት ለማሳካት ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የሚኖረን ግንኙነት ፋይዳው ከፍተኛ በመሆኑ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በመሆኑም ከሁሉም የጎረቤት ሀገራት ጋር የሚኖረን ግንኙነት በመተማመን፣ በመከባበርና በሌሎች ሀገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባት መርህ ላይ የተመሠረተ ይሆናል፡፡

ከሁሉም ጎረቤቶቻችን ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ የሁለትዮሽ (Bilateral) እና የብዙዮሽ (Multilateral) ስምምነቶችንና የትብብር መድረኮችን በመፍጠር መልካም እድሎችን በጋራ ለመጠቀምና ስጋቶችን ለመከላከል በከፍተኛ የኃላፊነት ስሜት መስራት ያስፈልጋል፡፡ ሀገራችን በአፍሪካ ቀንድ ካሉ ሀገሮች ጋር ስትወዳደር በኢኮኖሚ፣ በቆዳ ስፋትና በህዝብ ብዛት ታላቅ ሀገር ነች፡፡ ያለንን የተሻለ አቅም ተጠቅመን ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በጋራ በመስራት የህዝባችንንና የጎረቤት ሀገራት ህዝቦችን የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን እንቀይሳለን፡፡ ከአፍሪካ ቀንድ የልማት በይነ-መንግስታት (ኢጋድ)፣ ከምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ እና ከሌሎች መሰል ክፍለ አህጉራዊ ተቋማት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ የፖሊሲ ማዕቀፎች ተቀርጸው ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

## 4.3 ከአፍሪካ ህብረት እና ከአባል ሀገራቱ ጋር የሚኖረን ግንኙነት

1. ሀገራችን የአፍሪካ ህብረት ላይ ያላትን ተሰሚነት በመጠቀም በአህጉሪቱ ነጻ የንግድ ቀጠና እንዲመሰረት በማበረታታት ሀገራችን ከአህጉራዊ የኢኮኖሚ ትስስር የተሻለ ተጠቃሚ የምትሆንበት አሰራር ይዘረጋል፣
2. የአባይ ወንዝን በመጠቀም የሀገራችንን ልማት ለማፋጠን በተለይም ከአባይ ተፋሰስ ሃገራት ጋር በትብብር መስራት የሚቻልበት ሁኔታ ይዘረጋል፣
3. ከአፍሪካ ቀንድ የልማት በይነ-መንግስታት (ኢጋድ) እና ከሌሎች ክፍለ አህጉራዊ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በአካካቢያችን አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራሉ፣
4. በአፍሪካ ህብረት አስተባባሪነት በመካሄድ ላይ ያለው የአፍሪካ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የባህል ትስስር እውን እንዲሆን ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ አገራችን ከሂደቱ የተሻለ ተጠቃሚ እንድትሆን ይደረጋል፣
5. ለአንድ ሀገር ዘላቂ እድገት የባህር በር ያለው አስተዋፅዖ ጉልህ ነው፡፡ ይህን ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት ከሁሉም የጎረቤት ሀገራት ጋር ስትራቴጂያዊ ሽርክና በመፍጠር ሀገራችን አማራጭ የወደብ አገልግሎት በአስተማማኝ ሁኔታ እንድታገኝ ጥረት ይደረጋል፡፡

## 4.4 ከሌሎች የዓለም ሀገራት እና ዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚኖረን ግንኙነት

ዓለም ላይ ካለው ነባራዊ ሁኔታና ሀገራችን ካለችበት ጂኦ-ፖለቲካዊ ሁኔታ በመነሳት በተለይ በኢኮኖሚ፣ ዲፕሎማሲ፣ ወታደራዊ፣ የቴክኖሎጂና ፖለቲካዊ አቅማቸው ከፍተኛ ከሆኑ ኃያላን ሀገራት ጋር የሚኖረን ግንኙነት ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡ በተቻለ መጠን ከሁሉም ሀገራት ጋር ሚዛናዊና የሀገራችንን ብሄራዊ ጥቅም ባስከበረ መልኩ ግንኙነታችን እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ ከዚህ አንጻር ከአሜሪካን፤ አውሮፓ ህብረት፤ ቻይና፣ መካከለኛውና ሩቅ ምስራቅ ሀገራት ጋር የሚኖረን ግንኙነት ከየሀገራቱ ጋር የነበረንን ታሪካዊ ግንኙነት፣ ያለንን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የባህል ትብብር ታሳቢ ባደረገ መልኩ ተቀይሶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከተባበሩት መንግስታት እና ሌሎች ዓለም-ዓቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚኖረን ግንኙነት የሀገራችንን ብሄራዊ ጥቅም ይበልጥ በሚያስከብር እና ሀገራችን ለዓለም ሀገራትና ህዝቦች ሰላምና ልማት የድርሻዋን እንድታበረክት በሚያስችል መንገድ ተነድፎ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

እዝል የነፃነትና እኩልነት ፓርቲ መዝሙር

# የነፃነትና እኩልነት ፓርቲ መዝሙር

ሕብራችን ምሰሶ ሰላማችን ማገር
ሆኖ ሚያቆማትን የሁላችን ሀገር
ለማነፅ በወኔ ተነስተናልና
ይሁንታህን ቸረን ተከተለንና
ተከተለንና፡፡

ሁሉ ሰርቶ ሚያድር ወልዶ ሚስምባት
ተድላና ቸር ወሬ የበረከተባት
ፍፁም ሉዐላዊት የነፃነት ቅፅር
አልመናል እኛ ነገን በመነፅር
ነገን በመነፅር፡፡

ሰርክ የዘመርክላት
ሰው የመሆን ፍትህ
ሥጋ ለብሳ ህያው
እስከትቆም ከፊትህ
ተጭኖን የኖረው የፈርኦን ቀንበር
ከጫንካችን ወርዶ ወድቆ እንዲሰባበር
ምን መላ አለን ከቶ ካለመተባበር
ካለመተባበር፡፡

ላም አለኝ በሰማይ ህልምን ተመርኩዞ
እውን አይሆንምና የኩልነት ጉዞ
ያንድ ሰው ጥንድ እግር
ባንድ እንደሚራመድ
አብሮነትም ይህ ነው
ባላማ መዛመድ
ባላማ መዛመድ፡፡

ሕብራችን ምሰሶ ሰላማችን ማገር
ሆኖ ሚያቆማትን የሁላችን ሀገር
ለማነፅ በወኔ ተነስተናልና
ይሁንታህን ቸረን ተከተለንና
ተከተለንና፡፡

በርቅና ይቅርታ ድኖ ስለ መክረም
በተስፋ ሚበሰር የታሪክ መስከረም
እንዲጠባ ናፍቀን ቀምረን ሰሌዳ
ደርሰናል ደጃችሁ ላዲስ ቀን ማለዳ
ላዲስ ቀን ማለዳ፡፡

ከኢትዮጵያ ሰማይ ስር እንዳንድ እናት ልጆች
እኩል ተዘርግተው በሚያከብሩን እጆች
መታቀፋችንን በውል እስክናየው
ድምፃችን ነጎድጓድ ሠልፋችን ማዕበል ነው
ድምፃችን ነጎድጓድ ሠልፋችን ማዕበል ነው፡፡
ሠልፋችን ማዕበል ነው፡፡

ላምአለኝ በሰማይ ህልምን ተመርኩዞ
እውን አይሆንምና የኩልነት ጉዞ
ያንድ ሰው ጥንድ እግር
ባንድ እንደሚራመድ
አብሮነትም ይህ ነው
ባላማ መዛመድ
ባላማ መዛመድ፡፡

ማንነትህን በደል እምነትህን ጥፋት
አርጎ ያሳደደህ ለስርና ግርፋት
የእብሪትን ችግኝ ከስሩ ገርስሰን
ለመጣል ስንገፋ ክንድህን አውሰን
ክንድህን አውሰን፡፡

ሁሉ ሰርቶ ሚያድር ወልዶ ሚስምባት
ተድላና ቸር ወሬ የበረከተባት
ፍፁም ሉዐላዊት የነፃነት ቅፅር
አልመናል እኛ ነገን በመነፅር
ነገን በመነፅር፡፡